# ጅዳ ነኝ

ከፀጋ ዮሐንስ

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

በ1991 ዓ.ም. በንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ

የሽፋን ዲዛይን
ከትዕግስት ፍቃዱ

# መግቢያ

በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የተቀረፁት ገፀ ባህሪያት በገሀዱ ዓለም የሌሉ ፍፁም ልቦለዶች ናቸው:: የራሴንም ጨምሮ የማውቃቸው የስደት ጓደኞቼን ህይወት ምንም ያልነካ ሙሉ በሙሉ ልቦለድ ታሪክ ነው::

ታሪኩ የቆመበት ቦታ እና ባለታሪኮቹ የተንቀሳቀሱበት አካባቢ ግን ጅዳ እራሷ ናት::

ፀጋ ዮሐንስ

መታሰቢያነቱ የስደት ጓደኛዬ ለነበረችው ህይወቷን ጅዳ ውስጥ ላጣችው አስቴር _______ ይሁንልኝ::

## ምስጋናዬ

ይህን መጽሐፌን አሁን የሚገኝበትን የመጨረሻ ቅርጹን ይዞ እንዲወጣ ለረዱኝ ለእህቴ ወ/ሮ ምንያ ዮሃንስና ለአቶ ጌድዮን ተከላ ከፍተኛ ምስጋናዬ ይድረሳቸው::

# ጅዳ ነኝ

## ምዕራፍ አንድ

ለመጨረሻ ጊዜ ጥቁር ሻሽ አጠማጠም ተለማመድኩ:: ሻሹን አዟዙሬ መጠምጠሙ በቻልኩ ቁጥር በአጭር ጊዜ እራሴን የቻልኩ እየመሰለኝ በተስፋ ተሞላሁ:: ከአረብ አገር መጥታ የነበረችው የአጐቴ ልጅ በእጇ የሞላችው የወርቅ አንባርና የሰውነት ልስላሴ በአዕምሮዬ ብቅ እያለብኝ ጥቁር ቆዳዬን ጠላሁት:: በምትኩ ጅዳ ሄጄ ጠየም ያለ ቆዳ ያማረ ሰውነት ቅርፅና ቁመናን እንኳን ለግሶኝ በውበት ስምነሽነሽ ታየኝ:: እና ያኔ አዲስ አበባ ብቅ ብዬ ውበቴን በአገሬ እያበራሁ እንዴት እንደምስብ ቃኘሁ:: ይልቁንም የሻከረ ጥቁር ቆዳዬን ከአጐቴ ልጅ ቡናማ ለስላሳ ቆዳ ከርዳዳ ፀጉሬን በለስላሳው ዘመናዊ ቡናማ ፀጉሯ ባወዳደርኩ ቁጥር «እንዴ! በጣም ቀላች አማረባት:: መልኳም ተቀይሮ ውብ ሆናለች:: በፊት ከዚህ ስትሄድ አመዳም አልነበረችም እንዴ?! ሆሆ! እያቴ ሲተርቱ «ሰው ኑሮውን ይመስላል» ያሉት ልክ ነው ሆሆ!» እያለች በአድናቆት ትናገር የነበረችውን የእናቴ ድምፅ በጆሮዬ ያስተጋባና በውበት

ከእርሷ እንደምበልጥ እራሴን አሳመንኩ. . . ብቻ እዛ ልድረስ ብዬ ፀለይኩኝ::

ወር ሙሉ ያጐቴ ልጅ ያወራችልኝን የነዋይ ብዛት ገና ካሁኑ ምን እንደማደርግበት ሀሳቤን ሰረቅ እያደረገ የራሱ አድርጐታል:: በውነት ገንዘብ ምን ያህል እንደምወድ እስካሁን አላወኩም ነበር:: ያች ዘመዴ ላደረገችው የወርቅ ድርድር ክው ማለቴንም አልክድም::

በነጭ እምነበረድ የታነፁ ነጫጭ ህንፃዎች ከበዙበት ደስ የሚል ከተማ እራሴን ሳገኝ እግዚአብሔርን አመሰገንኩ:: አይኖቼ ከወዲህ ወዲያ እያማተሩ መንገዱን መብራቱን ህንፃዎቹን አልጠግብ አሉ:: በሰፊው የተዘረጋውን መንገድ መሀል ለመሀል የሚከፍል ብርሃን ነገር ከውስጥ ተቀብሮበታል:: ብቻ መንገዱ ከስፋቱ ከጥራቱ አይን የሚሞላ የሚለው ቃል ያንሰዋል::

አየሩ ግን ከበድ ያለ ነበር:: በሀይል እየተነፈስኩ ትንፋሽ እጥር ይለኛል:: ሁለቱን አገሮች ኢትዮጵያንና ሳውዲ አረቢያን በፍልስፍናዬ ሳስቀምጣቸው እንዲህ አድርጌ ነው:: ኢትዮጵያ በአየር በተፈጥሮ ስትበልጥ ይህችኛዋ ደግሞ በብርቅርቅናዋ ትበልጣታለች:: አዎ! ይህች ልክ እንደተኳለች በዕንቁ እንደተንቆጠቆጠች የራሷ ያልሆነ ውበት ያደመቃት ስትሆን:: . . . የኔዋ ደግሞ ምስኪን ውበቷን መደበቅ ይቀናታል:: ውበቷን ለማየት አየሯን መተንፈስ ያስፈልጋል:: ብቻ ለአሁኑ



ቁልጭልጩን መርጫለሁ:: ደግሞም የኔዋን ማን ይከለክለኛል?!

የጫኑኝ አረቦች በመጠየፍ እየተመለከቱኝ በአረብኛ ይንጣጣሉ:: እኔ ግን ያንድ ቃል ትርጉም ለማወቅ ትንቼአለሁ:: ገና ጅዳ እንደደረስኩ ሻንጣዬን ጐተት እያደረግኩ ፈዝዤ እያለሁ የአውሮፕላኑ ማረፊያ ፖሊስ «ያ ሁማራ» ብሎ ያለኝ በህይወቴ ለኔ ተብሎ የተወረወረውን የመጀመሪያ የአረብኛ ቃል . . . «ያ ሁማራ» «ያ ሁማራ»

ሰዎቹ ቤት እንደደረስን ፈረንጅ መሳዩ ሹፌር ሻንጣዬን ይዞ ተከተለን:: ፈረንጁን ሲሸከም ማየቱ አዲስ ነገር ቢሆንብኝም ወንዶችን ብዙ ማየት እንደማይፈቀድ ስለሰማሁ እርሱ ላይ ማፍጠጡን እየፈለግኩ ፈርቼ ተውኩት:: የአሰሪዎቼ ቤት እጅግ ያማረ ቤት ሆኖ አገኘሁት በፊልም ላይ ካየኋቸው ቤቶች ጋር ይማሰላል:: የዕቃዎቹ አቀማመጥ ለአይን ይመቻል::

ከአየር ማረፊያ ፓስፖርቴን ይዛ ያመጣችኝ ሴት ፊቷን ስትገልጠው እንደድምፅዋ አሮጊት አልነበረችም:: ይህችው ሴት በምልክት ጫማዬን እንዳወልቅ ነገረችኝ:: በቤቱ የነበሩት ሰዎች ሁላ እኔ ወዳለሁበት አቅጣጫ የተለየ ነገር እንዳዩ አይነት በጣም አፈጠጡ:: ከሰዎቹ አስተያየት በጣም መንከርፈፌን አወኩ:: ሁኔታዬን ለመሸፈን ፈጠን ብዬ ፈገግታ ሰጠኋቸው:: ሴትየዋ ፈጥና ተቆጣችና በተሰባበረ እንግሊዘኛ «ኖ ስማይል ውመን»

/ፈገግ የማትለዋ ሴት/ በእጇ ደግሞ ወደ ወንዱ እያሳየች የአጐቴ ልጅ ያለችኝን ረስቼው ኖሯል:: ደነገጥኩ:: ካሁን አሁን ወደመታረጃው ቦታ የሚወስዱኝ መስሎኝ ሰውነቴ ሲኮማተር ተሰማኝ:: ከደረጃው በኩል ብቅ ያለችው አሮጊት ሴት ልቤን አረጋጋችው:: «ያ ሚስኪና» እያለች በመራራት አየችኝ:: አረብኛ ከመቼው ተማርኩ:: ያለችው ገብቶኛል:: . . . ከአማርኛው ጋር አንድ የሆነ ቃል መሆን አለበት::

ቀጥሎም ሙሉ እቃዬን የያዘ ሻንጣዬን አይኔ እያየ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ በርሜል ውስጥ እንዲከተት ተደረገ:: አዳዲስ ቅያሪ ልብሶችና ጫማ ሳሙና ፎጣ ማበጠሪያ የጥርስ ብሩሽ አምጥተው ታጥቤ ለብሼው የነበረው ልብስም ሻንጣዬን እንዲከተል ሴትየዋ አስታወቀችኝ:: ብቻ ከሁለም የቆጨኝ እናቴ ደፋ ቀና ብላ ያዘጋጀችው ሽሮና በርበሬ እንደቆሻሻ ሲጣል ነው:: ገና እንደገባሁ ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማያውቅ አዲስ ስሜት ተሰማኝ:: . . . ባይተዋርነት . . . ቦታው ያንቺ አይደለም የሚል አይነት . . . እናም ጠላኋቸው:: ትንሽ እንኳን እንግዳ ናት የለም:: በእንደዚህ አይነት አቀባበል . . . አስደንጋጭ አቀባበል . . . ተቀበሉኝ አሰሪዎቼ::

አስተማሪያችን የነበረችውን ሕንድ የምትመስል ባንግላዲሻዊት ሴት የፅዳቱን ስራ ረጋ ብላ አስተማረችኝ:: ትንሽ ያስቸገረኝ ሥራ ቢኖር የቆጥራ /የወንዶች ሻሽ/ አተኳኮስ ነበር:: ይህ ቆጥራ ሁለት ዓይነት ብቻ ነው:: አንዱ ሙሉ ነጭ ሌላው እንደፊሊስጤሙ መሪ የቀይና



ነጭ ዥንጉርጉር:: ታዲያ ይህን ስስ ሻሽ ከአራት ማዕዘን ወደ ሦስት ማዕዘን ቀይሮ መተኮሱ ልዩ ዘዴ ያስፈልገዋል:: አለበለዚያ እየተዛነፈ /እየተዘናበለ/ ያደክማል:: በሰውዬው ጭንቅላት መሀል ላይ የሚውለውን መስመር ለማስመርም ካውያውን መጫኑ ቀላል አይደለም::

መጥረግ ማጠብ እቃዎችን ማፅዳት ከባድ አይነት ሥራ አይደለም:: በርግጥ አድካሚ ነው:: ግን የሰው ልጅ በቀላሉ የሚለምደው ብቸኛ ሥራ ይህ መሆኑ ነው:: እኔም በቀላሉ ተለማምጄ ከባንግላዲሻዊቷ ሰራተኛ ባላነሰ ፍጥነት ተፍ ተፍ ማለት ጀመርኩ::

ያበሻ ጆሮዬ በማይችለው ሁኔታ የሴትየዋ ጩኸት ያማርረኝ የጀመረው ገና በገባሁ ከጥቂት ሰዓቶች ጀምሮ ነበር:: ያበሻ ጆሮ ከሌሎች ጆሮ በምን እንደሚለይ ታውቂያለሽ? ቁጡ ነው:: ቶሎ ተቆጥቶ በንዴት ቷ ይላል:: ይህ ስለታማ ምላሷና ትዕቢተኛ አስተያየቷ እግሯ ስር ሆኜ ስትረግጠኝ የሚሰማኝ ስሜትን ይወልድብኛል:: ብቻ . . . ሙሉ ትዕግስቴን ለአካባቢዬ ሰጥቼ ነገሮችን ረጋ ብዬ ማየት ስጀምር አዲሱ እርምጃዬ ቀለል ብሎ ታየኝ::

የመጀመሪያ ደሞዜን ሳገኝ ከደስታ ብዛት እንቅልፍ አልወሰደኝም:: በጣም በጣም ተስፋ የሰጠኝ ደግሞ ሪያላቸው ወደኛ ብር ሲለወጥ እጥፍ የመሆኑ ነገር ነው::

ፐ . . . አልኩኝ:: ፐ ድህነት ባይ! ባይ! ቻው ደህና ሁን ድህነት::

እ! ለእናቴ ወርቅ ልብስ በያይነቱ . . . እ! ለራሴ መኪናና ቪላ ቤት ብቻ . . . ወንድሜስ አዎ ለሱ ሚኒ ባስ ውይ እህቴስ? አዎ ለሷ ደግሞ የፀጉር መሥሪያ ሙሉ እቃዎችን ገዝቼላት ፀጉር ቤት ሳይሻላት አይቀርም. . . አክስቴስ ምን ትለኛለች! ለሷ በቃ የሆነ ነገር . . . እ! አጐቴስ ይቀየመኛል. . .

እምን ስንት ዓመት መሥራት አለብኝ? ሦስት ዓመት እንደምንም አብቃቅቼ በቂ ጊዜ ነው:: ከዚያ እመለሳለሁ በጣም ናፍቄአለሁ:: ያኔ ተዲያ ሌላ ሰው ነኝ::

ደግሞም አለምኩ:: ቁምሳጥን ውስጥ ካየኋቸው የእመቤቴ የሀር ቢጃማዎች አንዱን አድርጌ . . . አገሬ ይመስለኛል ትልቅ ቪላ ቤት ውስጥ በሚደላ መቀመጫ ሆኜ ቴሌቪዥኑን እያየሁ . . . ከፊት ለፊቴ የተደረደረውን ነጭ ቸኮሌት እየበላሁ በፊልም . . . ስመሰጥ ክር የለሽ ዘመናዊ ስልኬን ይዤ ሥራ እንደበዛበት ሰው ወዲህ ወዲያ እያልኩ በሥሬ ከማስተዳድራቸው የፋብሪካዬ ሠራተኞች ጋር በትህትና ሳወራ . . . በቃ ምን ልበልሽ ህልሜ ድሎት አጥግቦኝ ያድራል:: ስነቃ ህልሜን እውን ለማድረግ ጠንካራ እግሮቼን በፍጥነት ከወዲህ ወዲያ እወራጫለሁ:: ብቻ ጨኸታማ አሰሪዬን ድንገት በጥዋት ነቅታ ካየኋት ለቀኑ ሙሉ መጥፎ እድሌ ምልክት ስለምትመስለኝ ደስ አይለኝም::



በሦስት ወሬ የዚያ ትልቅ ቤት ብቸኛ ሠራተኛ ሆንኩ:: ምክንያቱ የእመቤቴ ስስታማነት ነው:: ለኔ ትንሽ ገንዘብ ጨመረችልኝና ሙሉ ጉልበቴን ልሰጣት [illegible]ማማችኝ:: ባንግላዴሻዊቷ የሥራ ጓደኛዬ የእኔ መምጣት እንዳስደሰታት ሁሉ በጣም ተከፍታ ወደአገሯ ተጠረዘች /ተላከች/::

ሰሞኑን በሰበቤ ለተሰበረው የልብስ ማድረቂያ ማሽን ማሠሪያ የሁለት ወር ደሞዜ ተቆረጠ:: ሰርቶም እያለ ለመቀጫ ተብሎ ልብስ ለማስጣት በየቀኑ ሦስት አራቴ ፎቅ «ስጡህ» /የፎቅ መጨረሻ/ ስወጣ ፀሐይዋ ለማዩን ከትክታ ሰባብራ አናቴ ላይ ቧ ብላ የምትፈነዳ እስኪመስለኝ ድረስ ትጠቀጥቀኛለች:: አንድ ልብስ ለማስጣት አንገቴን ባንጠራራሁ ቁጥር ውስጧ የምላወስ ይመስለኛል:: የዚያን ያህል ጠራራ ፀሐይ መቼም ቢሆን አገሬ ላይ ሰፍሮ አያውቅም:: ሁሉም ተክል እርርር. . .ርር ብሎ ድርቅ ብሏል:: አረንጓዴ የሚባል ነገር የለም:: ላለመዋሸት አልፎ አልፎ ከተተከሉት አመዳም ቅጠላ ቅጠሎች በቀር . . እነርሱም ቢሆን በየቀኑ እንደጉድ የሚጠጡትን ውሃ ፀሐይቱ እየነጠቀች እንዳይሞቱም እንዳይኖሩም ሆነው መሀል የተንጠለጠሉ ቅጠሎች ናቸው:: ለአንድ ቀን ውሃ ቢቋረጥባቸው ምን ይሆኑ? ደግሞስ ውሃው ይጥማቸው ይሆን:: ያገሬን ውሃ ሳስታውስ ምራቁ አፌን ይሞላዋል:: ምራቁን በዋጥኩ ቁጥር ይበልጥ ይጠማኛል:: ውሃ የሚጠጣው እየተገዛ በመሆኑ አንድ ፕላስቲክ ውሃ ጠጣሽ ማለት አንድ

ጠርሙስ ከካከላ ጠጣሽ ማለት ነው። ዋጋቸው አንድ በመሆኑ እንደልቤ ውሃ አልጠጣም። የምጠጣው በስስት ነው። እስክጠግብ ውሃ ጠጥቼ ከዛም ፊቴ ላይ ጨብ ጨብ ለማድረግ ምን ያህል እንደናፈቅኩ አትጠይቂኝ። እናም ስዑዲ በረሃ ናት በበረሃ ውስጥ ህዝቦቿ ይንፈላሰሳሉ። ባማረ መኪናቸው ባማረ መልካቸው ባማረ ቤታቸው። እመኚኝ ምቾት ልብሱን ጠቅልሎ የገባው አረቦች ጋ ነው።

የጉደላቸውን ቀዘቃዛ አየር የሚያሟላ ማሽን አላቸው። የአየር ማቀዝቀዣው ከባዱንና ሞቃቱን አየር ቀይሮ ቀዝቃዛ አየር እቤት ውስጥ እንዲሰፍን ያደርጋል። መኪና ውስጥም እንዲሁ። የፀሐይዋ ብርታት የሚሰማው እንደኔ ልብስ ለምታሰጣዋና ለምስኪኖቹ ወዛደሮች ነው። ልብስ ሳሰጣ በተለያየ አቅጣጫ ለፎቅ ሥራ የሚሆን ድንጋይ ተሸክመው ገላቸው በላባቸው እየታጠበ ሲዋትቱ በየቀኑ አስተውላለሁ። ለሸክም ሥራ የሚሆን ግዙፍ አካል ያላቸውና መራራውን ፀሐይ የሚደፍሩት ሁለቱ ዜጎች ፓኪስታኖችና ግብፆች ብቻ ናቸው። አበሻማ በምን አቅሙ። ሚጢጢ ገላውን እንኳን ማወራጨት አይችልም እንደ ፀሐይዋ አቋቋም። ምን ያህል አጭርና ደቃቃ ህዝቦች እንደሆንን ታውቂለሽ? በርግጥ ከሕንዶች ብዙ አንተናነስም። ፊሊፒኖችንና ባግላዲሾችንም እንበልጣለን። ከነዚህ ከሚሸከሙት ህዝቦች እና ከአረቦች ጋር ግን የጉላ ልዩነት አለን።



ታዲያ ወዛደሮቹን ፓኪስታኖችና ግብፆችን የምታቀልጠውን ፀሐይ በድፍረት የተጋተሩትን ሳይ ኃይልና ጥንካሬን ይሰጡኝና ፀሐይዋ እንዳላቃጠለችኝ ሁላ አትት. . . ትት ሲበርድ እያልኩ እወርዳለሁ።

ደሞዜ ተቆራርጦ እንዳያልቅ በየቀኑ ጥብቅ ጥንቃቄ በቤቱ እቃዎች ላይ አደርጋለሁ። እመቤቴ ብዙ ሀብት ቢኖራትም ለሰበርኳት ስኒ እንኳን ምህረት አታደርግልኝም። በተለይ በቀደም እለት ገዝተዋቸው የመጡትን የበረንዳ አበባ ማስቀመጫ ባዞች ስወለውል እጅና እግሬ መንቀጥቀጥ ጀምረዋል። ሲገዙ አብሬአቸው ነበር። ከባዞቹ ውስጥ አንዷን ብሰብር እድሜ ልኬን ብሰራ እንኳን ለመክፈሌ እርግጠኛ አይደለሁም።

እመቤቴ አብዛኛው ጊዜዋን የምታጠፋው በየሱቆች እየዞረች በመግዛት በመግዛት በመግዛት ነው። በዚህ ልምዷ እኔም ብዙ ብዙ ሱቆች እያየሁ ክርፍፍ እስክል ተደንቄአለሁ። በሱቆቹ ጥራት። ከንደራ በሚባለው ቦታ ያለውንም የጌጣጌጥ ሱቅ አየሁት። በወርቁ ብዛት ተደንቄ ከሚገባው በላይ አይኔን ስለተከልኩ እራሴን አመመኝ። ወርቆቹን ለማድመቅ የበሩት ፓውዛዎች ሀይለኛ በመሆናቸው ልቤን ወደላይ አለኝ። እንደቋንጣ በወፍራሙ የተንጠለጠሉት ወርቆችና የአልማዝ ፈርጦች ብልጭልጭነታቸው ውስጤ ሰርጎ እየገባ መቆም አልቻልኩም። አልማዞቹም ብርጭቆአማ ስቦታቸው የሴት ልብን ይፈታተናል። እመቤቴን ጨምሮ ብዙ ሴቶች

በአካባቢው የሚርመሰመሱትም ምክንያቱ ይኸው መሆኑ ነው።

ለምግብ ገበያ ስንወጣም በአገራችን የሌሉ ምግቦች ይበዛሉ። ስማቸውን እንኳን ለምቼ የማላውቀው ፍራፍሬዎችም ብዙ አይቼአለሁ። የቅጠላ ቅጠሉቹም ብዛት ለቁጥር ያዳግታል። አረቦቹ አመጋገባቸው ሰፊ ነው። ባለፈው ጊዜ የምበላው ደረቅ ዳቦ ብቻ ስለነበር በጣም ከስቼ ነበር። የወተቱም ጣዕም የተለየ ስለሆነ የግድ አፍንጫዬን አፍኜ እንደኮሶ በግድ ከጉሮሮዬ ሳወርደው ከርሜ ቀስ በቀስ ለመድኩት። «በወረቃ አይነቡ» /በወይን ቅጠል/ የሚሰራው «ማህሺ» ተብሎ የሚጠራው ምግባቸው እጅ እንደሚያስቆረጥም ለማወቁ ጊዜ ፈጅቶብኝ ነበር። በኋላ ግን በጣም ጣፈጠኝ። በወይን ቅጠሉ ውስጥ በቅመምና በሌሎች አጣፋጭ ነገሮች ያበደ ሩዝ ይጠቀለልና በልዩ ዘይታማ ውሃ እንዲበስል ይደረጋል። ይህን ዘዴ በጥቅል ጎመንና ዝኩኒ ውስጡን ቦርቡረው ሩዙን በመጠቅጠቅም ይጠቀሙበታል። እኔ ታዲያ ቦርቡረው የከተቱትን ሩዝ ቦርቡሬ እበላና የወይን ቅጠሉንም ሆነ ዝኩኒውን ንክች አላደርገውም። የጅብ ጥላው ሾርባና «ሞለኪያ» የሚባለውን ምግብ «ባሚያን» ጨምሮ ዝልግልጋማ ውሃቸውን በማየት ብቻ ብጠላቸውም ብዙም ሳልቆይ ቀስ በቀስ ለምጄአቸዋለሁ። እንደውም አጣጥማቸው ጀምሮአል።

ልለምደው ያልቻልኩት የእመቤቴን ቁጣ ነው። ተሳስታ እንኳን እንደሰው አይታኝ አታውቅም። ሲሰራ



እንደማይደክመው ብረታማ አካል አድርጋኝ እንደጉድ እያሠራችኝ ምላሷን አትሰበስብም።

ለቁጣ ምክንያት ፍለጋ ሁሌ ስትጥር ሰሞኑን ጥሩ ምክንያት አገኘች። ወጥ ቤት ሳህን ፍለጋ ስትንጐዳጐድ በሥራዬ የምታግዘኝን ቀይ የሸክላ ድስት ሰበረች። በነጋው የሚጠብቀኝን ንዝነዛ ልክ ኳ ብሉ ሲሰበር አውቄዋለሁ።

ይህች ሸክላ ለተዋጣ የከፍያ አተካከስ የዘየድኳት አጋዥ ድስቴ ነበረች። የዚች ድስት ስፋትና ቁመት ከጌታዬ ጭንቅላት ጋር እኩል ስለሆነ የጌታዬን ጨርቃማ ከፍያ ስተኩስ ድስቷን አለብሳትና ያለምንም መስመር ቀጥ አድርጋ ትወጥርልኝና ባጭር ጊዜ ተኩሼ እጨርስ ነበር።

«ዛሬ የከፍያ አተኳኮስሽን ባሌ አልወደደውም እንደገና ተኩሺው» የጨኸት ትዕዛዝ ተከተለኝ። የተኩሱና የድስቷ ጉዳይ አላስፈላጊ ንግግሮችን እየጨመረብኝ መጣ። ተመሳሳይ ድስት ለመግዛት ምንም ዕድል አላገኘሁም።

«ሰሞኑን ሥራሽ ሁሉ የይምሰል ነው። መለገም ጀምረሻል። ከዳማዎች መለገም ከጀመራችሁ አትቻሉም። ስለዚህ ከፍያ አጨማዶ በመተኮስ ጥጋብሽን ጀምረሻል ሥራሽ ሁሉ አልጥም ብሎኛል ሳሎኑን በትክክል አላፀዳሽውም። የሸቶ መደርደሪያዬን ካፀዳሽ በኋላ ሽቶዎቹን እንደነበሩ አልደረደርሽም . . . ትሠሪ እንደሆነ

እንደበፊትሽ ሥሪ አለበለዚያ . . . » የስድብ ጋጋታም አወረደች::

ወጥ ቤት እያለን አጠገቤ ቆማ አከታተፌን ስታይ ስለነበር ስርበተበት የያዝኩትን ቢላዋ ጣቴ ላይ አሳረፍኩት:: ደሜ ቡልቅ ሲል የምታዝንልኝ መስሎኝ እንባዬን አቀረርኩ:: ያ ደደብ የአውሮፕላን ማረፊያ ፖሊስ መጀመሪያ ቀን ሲነጅሰኝ ያለኝን ቃል ደጋግማ አለችው::

«ያ ሁማራ» /አህዮ/ ደምሽን መሬት ላይ አንጠባጥቢና ወየውልሽ ነገርኩሽ ብላ ተንጣጣች:: ኧረ የሰው ያለህ . . . ደሜን እንደዚያ ሳዘራ . . . ጨከነች:: በእልህ ያቀረረ እንባዬን ዋጥ አደረግኩት::

ሁለተኛ ጨኸቷ እንደሚረብሸኝ ፊቴ ላይ ማየት የለባትም:: ስትሰድበኝ የመከፋት የማዘን ሁኔታ ሳላሳይ እንደውም ከራ ማለት እንዳለብኝ ወሰንኩ:: ደግሞ ያ ፖሊስ ተብዬው አይቶኝ አያውቅ የት አውቆኝ አህያ ብሎ ሰደበኝ?! ይህቺስ መቼም ገረዷ እንደሆንኩ እና እንደዚህ አይነት ቃላቶች ለኔው እንደተፈጠሩ አድርጋ አንጼ አዕምሮዋን መርዛለች::

የልምምጫው ነገር አላዋጣም:: እንደማያስብ እንሰሳ ስለሚያዩኝ እኔም እንደማስብ እንስሳ ሆንኩላቸው::

እንግዳ ሲመጣ የሚያቀርቡት የክብር የሻይ ዕቃ ስብስብ አለ:: ትሪ በትሪው ላይ ያማረ የሀገር ጨርቅ ዳር ዳሩ የተጠለፈ . . . በጨርቁ ላይ የሲኒ ማስቀመጫ:: በያንዳንዱ የሲኒ ማስቀመጫ ላይ በትንንሹ ተቆራርጠው



የተጠለፉ ትናንሽ የሀገር ቁራጭ ጨርቆች ይደረጋሉ:: ለስኳር ማስቀመጪያውም የራሱ የሆነ ማዳመቂያ ጨርቅ ተጠልፎለታል:: ትናንሽ ማንኪያዎችም በቦታቸው በቁንጥ ማስቀመጥም ይጠበቅብኛል:: የሻይ ጀበናውን የሚጀቡንና በዚያውም የሻሂውን ሙቀት እንዳይወጣና ሻይው በቶሎ እንዳበርድ የሚያደርገው ጀቧኝ ጨርቅ ከስኒ ማስቀመጪያው ጋር ተመሳሳይ ከለርና አጠላለፍ አለው:: ታዲያ ይህን ሁሉ ድርድር ለመማር ሶስት ቀን ፈጅቶብኝ ነበር:: በሙከራዬ ሰዓትም ወይ የጀበናውን ልብስ ወይ የትሪውን እረሳለሁ:: እኔ ይኸው ነኝ ቀልቤ ካልወደደው ቁም ነገር ብዬ ካልቆጠርኩ እረሳለሁ:: ይህ ለኔ ምንም ያልመሰለኝ የሻይ ሽንሽናሽንሽን ወሳኝ የእንግዳ አቀባበል ነው. . . ለነርሱ::

የሚያከብሩት እንግዳ ፊት የእንግዳ መቀበያ ሽርጣም ዩኒፎርሜን ለብሼ ኩስ ኩስ ስል ብዙ ነገር ረሳሁ:: ጉድ የሚያሰኝ ስህተት ሰራሁ:: . . . የሻይውን ጨርቅ ረሳሁ:: እዳር አላደርኩም:: ሴትየዋ እንግዶቿን ጠርታ ኩሽና አስገብታ ምን ያህል የተሟላ የሻይ ዕቃ እንዳላት ልታሳያቸው ምንም አልቀራትም:: አልገባኝም እንጂ ለዚያ ምሽት ብላ በልዩ ሁኔታ ያሰፋችው የሻይ ጀቧኝ ነበር:: ኡ. . . ሳያዩት በመሄዳቸው ብግን ብላለች:: ንዴቷን ልትወጣ እንደጥሬ ግፍተራ ማመናጨቅን በሚገባ ተጠቀመች::

ይህን ቂም አድርጋ ስትተነኳኩሰኝ መረረችኝ:: እንደለመደችው ባሏ በሌለበት ጥፊ ሰነዘረች:: ልስልስ

እጇን ያዝ አደረግኩና አጠፍ ሳደርጋት ትል አክለች:: አሳዘነችኝና ተውኳት. . . አበሻ አይደለሁ:: ባኗ እንዳይመጣብኝ ተቻኩዬ ጥቁር ልብሳቸውን /አባያ/ ለበስኩ:: እንዴ ስለተሳሳትኩ የእመቤቴን እጅ ስለጨመደድኩ የሚደርስብኝን እግዜር ይወቀው ቶሎ ከዚህ ቤት መውጣት እንዳለብኝ ወሰንኩ::

የታክሲ ብር አምጪ ብዬ አፈጠጥኩባት:: ስትርበተበት ተመልክቼ ለመቆራረጥ እንዲመቻት እኔው ጋር ይሁንልሽ ብላ ያልሰጠችኝን የአራት ወር ደሞዜንም ጠየኳት:: ምንም እንቢታ ፊቷ ላይ ሳይታይ ሳንቲም ሳይቀር ቆጥራ ሰጥታኝ ለእኔ ምላሷ ፈፅሞ አውጥቶት የማያውቀውን ውድ ቃል «ሹክረን» /አመሰግናለሁ/ አለችኝ::

ከቤቷ ከመውጣቴ በፊት «ፖሊስ ብትጠሪ ኤንባሲ ሄጄ እጄን በቢላ ቆረጠችኝ እላለሁ:: ዝም ብትይ ይሻልሻል:: ለእልህ ለእልህ ከኔ አትብሽም . . . እኔ ጥቁር ነኝ እ! ያንን አትርሺ» አልኳት:: እንግሊዘኛዬ እንደገባት ቶሎ ቶሎ ራሷን ነቀነቀች:: ልሰድባት አፌን ከፈትኩ::

«ያ ሁማራ እ የማታስቢ ጨካኝ» ብዬ ትንሽ እንደተራመድኩ «ያ ከልባ» /ውሻ/ አልኳት:: «ደግሞ እኔ ላይ በሠራሽው ግፍ ልክ መካ ሄደሽ ጠጠር ብትወረውሪ በፅኑ እንዲቀጣሽ ስለምፀልይ ምህረት አያደርግልሽም» አልኳት:: በመሀል በመሀል አማርኛ ቃል ሳላስበው እያመለጠኝ በንዴት ሁሉ ነገሬ ተወራጨ:: ስለእስልምና



ሀይማኖትና ስለመካ ይህን ያህል ባላውቅም አገሬ እያለሁ ጐረቤቴ የነበሩት ሀጂ ሙስጠፋ ወደ መካ የሀጅ ጊዜ የመሄዳቸውንና የጠጠሩን ነገር እናቴ በአድናቆት ስታወራ ሰምቻለሁ::

ኤንባሲ ድረስ ባለታክሲው አደረሰኝ:: የኤንባሲው ጠባቂ ፊቴን ብቻ አይቶ ያለምንም ጥያቄ አስገባኝ:: በማዘን ስላየኝ ብሶቴን አገነፈለብኝ::

«እባክዎ ይርዱኝ» አለቀስኩ

«እኔ ምንም ልረዳሽ አልችልም ግን ሊረዱሽ የሚችሉ የሚጠባበቁ ብዙ ሰዎችን በዚህ ህንፃ ውስጥ ታገኚአለሽ ግቢ!»

ከጐኔ በእርምጃዬ ልክ እየተራመደች ንግግሬን ቀስ እያለች የሰማች ልጅ በፈገግታ ቀረበችኝ::

«እንዴት ነሽ? ቅድስት እባላለሁ::» ለዚህች ልጅ ብዙ የምላት እንዳለ ተሰማኝ:: ያች ጠባብ ጊቢም ያገሬ ንፋስ ይነፍስባታል:: ከመጣሁ ለመጀመሪያ ጊዜ አማርኛ ሰማሁ::

«ደህና አይደለሁም:: በየቀኑ እየሞትኩ ነው:: ወደቤቴ መሄድ እፈልጋለሁ:: በዚህ ኤንባሲው እንዲተባበረኝ ነው የመጣሁት»

ቅድስት ዞር ዞር ብላ አካባቢዋን አየችና «ከኔ ሌላ ወደአገርሽ መመለስ እንደፈለግሽ እዚህ ግቢ ለሌሎች ተናግረሻል?»

«ገና መምጣቴ ነው። አንቺም እንደኔ በችግር ነው የመጣሽው አዲስ አበባ ልትመለሺ?!» ፊቷ እዘን አለ።

«እኔ እንኳን አባቴ ስለሞተ ለእናቴ የአባቴን ወራሽነት አልቃወምም የሚል ህጋዊ ወረቀት ላስፅፍ ነው የመጣሁት።»

«አዝናለሁ አባትሽ እዚህ እያለሽ ነው የሞቱት?»

«እዎን ከሁለት ወር በፊት . . . እኔ እዚህ ዓመት ከምናምን ሆኖኛል።»

ለቅፅበት ታየኝ በዚህ በስደት ችግር ላይ የአባት ሞት። ዘገነነኝ ደግሜ ማዘኔን ነገርኳት።

«አሁን የረጋሽ ትመስያለሽ። ይህ ሁላ እንባ ለምንድን ነበር። በዓለም ላይ ያለ ምንም ችግር ያን የሚያክል እንባ አይገባውም ገባሽ! ደግሞ ይህን ንፁህ ጉንጭ ለምን በእንባሽ ታበላሺዋለሽ? እንባሽን ማድረቅ ነበረብሽ እዚህ አገር ከመምጣትሽ በፊት። ምክንያቱም ያንቺ ያልሆነ ቦታ ላይ ብዙ የሚያስለቅሱ ነገሮች ይገጥሙሻል።»

ቅድስት ማፅናናት ትችልበታለች። በመጠኑም ቢሆን ጥንካሬን ሰጠችኝ።

«ጭራቅ ከሆነች ሴት ጋር ሥራ ልሠራ በኮንትራት መጣሁ» ሴትዮዋ በጣም ክፉ ነች። እንደሰው ሳይሆን እንደዕቃ ነው የምታየኝ። በቃ በድሮ ጊዜ እንደተሸጠች ባሪያ አድርጌ እራሴን እንድቆጥር



አደረገችኝ። ይህንን መቋቋም አልቻልኩም። ታውቂያለሽ በጥፊ ሳይቀር ትመታኛለች።»

ቅድስት ነገሩ ያስደነቃት አትመስልም። ከዚህ በፊት ከሌሎች ወይም እራሷ የጥፊውን ጉዳይ ሳታውቀው አትቀርም። አይኗን ወደ መሬት ተክላ

«አንዳንዶቹ እኛን እንደዛ ነው የሚያስቡን። ግን ሁሉም አይደሉም። ጥሩዎችም አሉ። እኔ ለምሳሌ ካንቺ የከፋ ሥራ ነበረኝ አሁን ደግሞ በጣም ጥሩ ሰዎች ጋ እየሠራሁ ነው። እኛ በአገራችን ብቻ ነው ክብር ሊኖረን የሚችለው። በሌሎች አገሮች የተሰደዱ ጓደኞቼ እንደዚህ እንደኛ በጣም አይገዙ እንጂ ሁሌ ያነሰ ቦታ ነው ያላቸው። አሁን አንቺ ስለመብትሽ እርሺ. . . ማሰብ ያለብሽ እንዴት ቶሎ አገርሽ የምትገቢበትን ሁኔታ ነው። እዚህ የመጣሺው ገንዘብ ለማግኘት ነው። መሥራት አለብሽ ጠንካራ ሁኚ ተሸቀዳድመሽ ባዶ እጅሽን አገሬ ልግባ ብለሽ አትወስኚ የተሻለ ነገር ይዘሽ ሂጂ ትንሽ ከሠራሽ ቤተሰብሽን ልትረጅበት የምትችይበትን ገንዘብ ልታገኚ ትችያለሽ። እኛ ሁላችንም ጓደኞቼን ጨምሮ የመኖሪያ ፈቃድ የለንም። ፖሊስ እስኪይዘን ተደብቀን እንሠራለን። ያች የምታሠራሽ ሴትም ልታገኝሽ አትችልም። ሥራ ለማግኘቱ ሁላችንም እንረዳሻለን። ለጊዜው ከኔ ጋር እቤቴ ልውሰድሽ የቡና እቃዎች አሉኝ። ቡና እያፈላሁልሽ ስለነገሩ ትወስኛለሽ እመኚኝ ሀሳቤ ደስ ካላለሽ መልሼ እኔው እራሴ አመጣሻለሁ . . .» አመንካት…

# ምዕራፍ ሁለት

የረዳችኝ ልጅ ቅድስት ከሌሎች እኩዮቼ አበሾች ሴቶች ጋር አስተዋወቀችኝ:: ገና ሳያቸው አዲስ አበባ የመመለስ ሀሳቤን ቀየርኩ:: ሁሉም በሀዘኔታና በፈገግታ ተቀበሉኝ:: ሁለት ሁለት ስም አላቸው:: በቀልድ የእስልምና ስማቸውንና እውነተኛውን አስተዋወቁኝ:: ሳባ /ሰባህ/፣ አበባ /ሳልዋ/፣ ዘመናይ /አይሻ/፣ ጽጌረዳ /ጀሚላ/::

ጀሚላና ሰባህ ከቅርብ ቦታ እንጀራ ለኔ ሲሉ ሊገዙ፣ ሳልዋ ሽሮ ልታበስል ኩሽና አይሻ ደግሞ ቡና ልታቀራርብ ተበታተኑ::

አራት በሶስት እርምጃ የምትገመተዋ ጠባብ ክፍል ብዙ ፍቅር ያለባት ትመስላለች:: ተመኘኋት:: ጐኔን የማሳርፍበት ትንሽ ቦታ ቢሰጡኝ ብዬ ፀለይኩ::

አዲሱ ሕይወቴ ከአበሾች ጓደኞቼ ጋር እንደቀልድ ተጀመረ:: የክፍሉ ዋና ተከራዮች ቅድስት ሰባህና ጀሚላ ናቸው:: አይሻና ሳራዋ የጀሚላ ጓደኞች ናቸው:: እዚህ የመጡትም አዲስ ቤት ለመከራየት እያፈላለጉ እስኪያገኙ ድረስ ብቻ ነው:: ቅድስት እንደክፍሏ አባል ወሰዳኛለች:: እኔም ጥገኝነት እንዳይሰማኝ የሚከፈለውን ከፈልኩ:: እነ አይሻ እስኪሄዱና ክፍሏ ቀለል እስክትል እኔንም ጨምሮ



ትልቁን ቤት በአጋማው /የመኖሪያ ፍቃዱ/ ከተከራየው ሰውዬ መደበቅ ነበረብን:: ሰውዬውና ሚስቱ ካንድ ልጃቸው ጋር ሲመጡ . . . የሚመጡበት ጊዜ የታወቀ ስለሆነ . . . ሲመጡ ጠባቧ ክፍላችን ትዘጋለች:: ሙክ ብሎ ለመሳቅም ሆነ ለማውራት የሚችሉት ቅድስት ሰባህ እና ጀሚላ ብቻ ነበሩ:: ሌሎቻችን እንታፈናለን::

ጀሚላ አይሻና ሳልዋ የሆነ የሚያመሳስላቸው የሚያጣምራቸው ነገር አላቸው:: ሰባህ ወደ ቅድስትም ወደነአይሻም ታወላውላለች:: ይህች ቅድስት ግን የተለየች ናት::

እድለኛ ሆንኩና ገና ሳምንት ሳይሞላኝ የቅድስት ዘመድ የሆነች ሴት ትወልድና በሥራ እንድረዳት በፊት የሚከፈለኝን ደሞዝ እንደምትከፍለኝ ተዋውላኝ ሥራ ጀመርኩ:: ለዚያውም ሀሙስ ለእረፍት ወጥቼ አርብ እገባለሁ:: እረፍቱ ብርቅ ሆነብኝ:: እውነቱን ለመናገር ሥራ የምሠራ መስሎ አልታየኝም:: የምታዘዘው በአማርኛ ነው:: ልክ ቤተሰቤ መሀል እንዳለሁ ዓይነት ተሰማኝ::

ለእረፍት ስወጣ እነ አይሻ ቅድስት ወጣ ስትልላቸው ቁጭ አድርገው ይመክሩኝ ነበር:: እዚህ አገር አበሻ ሆኖ አበሻ ቤት መሥራት እንደውርደት መቆጠሩን ሊያስረዱኝ ይሞክራሉ::

«ደሞዙ ዝቅ ያለ ነው:: በዚያ ላይ እንዴት አበሻ ቤት ትሠሪያለሽ? ወደ አገርሽ ስትሄጂ ይቆጭሻል:: አንድ

ቀን መንገድ ላይ ትገናኙና 'ይህችን እኮ ሳሠራት ነበር' ብላ ትጉርርብሻለች:: አረብ ቢገዛሽ ይሻላል» እያሉ:: አበሻዋ ሴት ከአራስ ቤቷ ስትወጣ በሰላም አሰናበተችኝ:: እነ ቀድስት ለዕረፍት ሲመጡ በጣም ደስ የሚል ጊዜ እናሳልፋለን:: እነ አይሻ ሳልዋና ጀሚላ ግን አንዳንዴ ማታ ላይ ብቻ ይወጡና ይመለሳሉ:: የተሻለ ሥራ እንደሚያፈላልጉ ይነግሩኛል:: ምሽዋር /የሆነ የሚደረስ ቦታ/ አለን ብለውም ሲወጡ ተቆነጃጅተው ነው::

ጀሚላ በቅድስት ታሾፋለች::

«የቅድስት ህልም "ረኢስ ከዳማ" /የገረዶች አለቃ/ ለመሆን ነው:: ለዚህ ነው በአንድ ቤት የሙጥኝ ብላ የተቀመጠችው::» በቀልዷ እንስቃለን::

«እንደናንተ የማይመስል ህልም ከማለም መሆን የሚችለውን ማለም ይሻላል:: እንደ እመቤቴ ልጅ ከማለም ደግሞ ይሰውረኝ!»

ባንድ ድምፅ ጠየቅን «ደግሞ እሷ ምን አጥታ ታልማለች?»

«ያላትን እንዲያሳጣት!»

«ምን!» የሆሆታ ሳቅ ሳቅን

«አልነገርኳችሁም! የምትገርም ልጅ ናት:: በቀደም አዝና አገኘኋትና ምን እንደሆነች ጠየቅኳት:: ምክንያቷ አስቂኝ ነበር:: 'አላህ ድሆችን ይወዳል' ሲሉ አልሰማሽም? ታዲያ ሀብታሞች አያሳዝኑም?» ብላ ነበር ያዘነችው:: እኔ በሆዴ «አቤት እናንተ ሀብታሞች ሁሉን ነገር የራሳችሁ ማድረግ ትወዳላችሁ:: እኛ ድሆች ባንድ አምላክ ፍቅር በንብልጣችሁ እናንተ በምድር የምታሳልፉትን ደስታ ማካካሻ አንድ የተስፋ ቃል ቢኖረን . . . አምላክ እናንተን ወደ እያለም . . . ትመቀኙብኛላችሁ» እያልኩ አጉተመተምኩ:: እንደገና ንግግሯን ቀጥላ ምን ትል መሰላችሁ . . . . «ኤዲ ሜርፊ የሚሰራበትን የአሜሪካ ፊልም አላየሽም?! ወጣቱ የንጉስ ልጅ ከንጉሳዊ ኑሮው ጠፍቶ የድህነት ጣዕምን ማየቱ እንዴት እንዳስደሰተው!!! . . . . እኔ ሁሉ ነገር አለኝ:: በልጅነቴ እንደሌሎች ሕፃናቶች በመጫወቻ ከማለሜ በፊት ቤተሰቦቼ ያመጡልኛል:: አያናድድም!» አለችኝ ብላ ቅድስት ስቃ ሳትጨርስ:-

አይሻ አፏን አጣመመችና «ለምን እንዲህ ስትቀብጥብሽ በጥፊ አትያት? ወላጆቿ ሰጥተዋት የማያውቁት ነገር ቢኖር ጥፊው ብቻ ነው:: ሞልቃቃ!»

«እንዴ ታዲያ ምን አናደደሽ?» አይሻን አበሸቅናት

«የማይመስል ነገር ስትል ነዋ! ያች ሚጢጢ አረብ::»

«እኔ ግን ምን አልኳት መሰላችሁ?!» ቀጠለች ቅድስት «ማለምሽን ሳታውቂ በድህነት እያለምሽ ነው:: አላህ ደግሞ ምኞትን እውን ያደርጋል:: አንድ ቀን ሁሉን ነገር አጥተሽ በደስታ እፎይ ትያለሽ:: ከዚያ የተመኘሽውን

የኛን የድሆችን ስሜት ህልም ታገኚና ታመሰግኛለሽ:: ግን ላስጠንቅቅሽ ድህነት የሚጥመው ባየሽው የአሜሪካ ፊልም ላይ ብቻ ነው»

ሁላችንም ባንድ ድምፅ:-

«ሀራም! /ግፍ ነው/ ሀራም!» ብለን ያለቻትን ነገር አወገዝን:: የድሀ ቁጥር ቢጨምር ምን ልንጠቀም?!::

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

ያለሁበት ሰፈር "መርካቶ" የሚል ቅጥያ አለው:: ጅዳ ያለ አበሻ አብዛኛው የሚኖረው በዚህ አካባቢ ነው:: ቡዋዲ ይባላል:: መቼም አበሻ በአንድ አካባቢ መሰባሰብ ይወዳል:: የአበሻ ወንዶችም ተሰባስበው የሚያወሩበት «አፍሪካ ሻይ ቤት» የሚባል ሻይ ቤት አለ:: እዚያው ምግብ የዶሮ ወጥ እና እንጀራ ይሸጥበታል:: አጠገቡ ደግሞ ሌላ አነስተኛ መደብር አለች:: ውስጧ ቡና ዕጣን ምናምን ይሸጥባታል:: ለዚያውም ቡናው ደረጃ አለው:: የሀረር ቡና የከፋ ቡና እየተባለ:: የጤፍ እንጀራም እዚህ ሱቅ ይገኛል:: ግን ስለሚወደድ ለበዓል ጊዜ ብቻ ነው እኛ የምንገዛው:: ሌላ እንደእንጀራ ብዙ አይኖች ያሉበት እንጀራ መሳይ ነገር ይሸጣል:: እኛ የምናዘወትረው ይኼንኑ እንጀራ ነው:: የሚገበየው ሁሉ አበሻ ስለሆነ አገር ቤት ያለሁ ይመስለኛል:: እዚህ ሠፈር ስመጣ ትንሽ



ሳይርቅም የሀረር ስጋ የሚል ስም ያለው ስጋ ቤት አለ:: መርካቶ ኢትዮጵያ የሚለው ሱቅም ውስጥ ጀበና ምናምን የባህል ዕቃዎች የሚገኙበት ነው::

አንዳንዴ ምንም ሳልገዛ እዛ አካባቢ እንደሞኝ አንዣብቤ እመለስ ነበር:: በቃ ደስ ይለኛል::

አለፍ ብሎ ሱቅ አልበዋዲ /የቡዋዲ ገበያ/ ይገኛል:: ብዙ ነገሮች በረከሰ ዋጋ የሚገኙበት ሱቅ ነው:: በጣም ሰፊ ነው:: ትልቅ የገበያ ቦታ ነው:: ታዲያ አበሾችና ሕንዶች፣ ባንግላዴሾች ፊሊፒኖች ሱዳኖች . . . የመሳሰሉት ድሀ ስደተኛ ሕዝቦች የሚገበያዩበት ቦታ ይኸው የቡዋዲ ገበያ ነው:: አረቦቹ ታዲያ በዚህ የገበያ ቦታ ሲያሾፉ "ቦምቤ" ብለው የሕንዱን ከተማ ይወክሉበታል:: የሦስተኛው ዓለም ግብይትም ብለው ይጠሩታል:: በገበያው ቦታ ያሉት ሻጮች አብዛኞቹ የመኖች ናቸው:: እዚህ ሱቅ ስንሄድ ፊታችንን አንሸፍንም:: ለነገሩ ፀጉርና አንገት በደንብ ከተሸፈነ የሱዑዲያ ተወላጆች ላልሆኑት ምንም አይደለም:: አይንና አፍንጫን ማሳየት ይፈቀዳል:: ከአበሻ ወንዶች ጋር ስንተያይ ታዲያ መፋጠጥ ነው:: ሰላምታ ንግግር የለም:: አልፎ አልፎ በየሱቁ በራፍ ላይ «በአሻራ በአሻራ ሪያል ኩሉ አሻራ በስ» /የሁሉም ዋጋ አስር አስር ሪያል ብቻ/ እያሉ በመጮህ ገዢ የሚጣሩ አበሾች ቢኖሩም ሥራው ስለሚያሳፍራቸው ሦስት ቀን እንኳን ሳይሰሩ ሥራውን ለሕንዶች ይሰጣሉ:: ወይ ደግሞ በዑምራ አካባቢ የመጡ አዲሶች ይሆኑና እዚያው መንገድ ላይ ፖሊሶች

ይጠርዟቸዋል። ምን ፖሊስ ቢኖር ግድ የማይሰጣቸው ደፋሮቹ አበሾች ደግሞ በድብቅ ያጣሩትን ካቲካላ በውሃ ፕላስቲክ እያደረጉ በጀርባቸውና በሆዳቸው ሸጉጠው መንገድ ላይ ይንቀዋለላሉ። መጠጥ ክልክል ስለሆነ አረቦች ይህ ካቲካላ ብርቃቸው ነው። በውድ ይገዙታል። ታዲያ የሚገርመኝና መልስ ያጣሁለት ጉዳይ የመጠጡ ሻጭና ገዢ እንዴት እንደሚገናኙ ነው። የተገኙ ጊዜ ጀርባቸውን አርባ ጅራፍ ይላጡና ወደ አገራቸው ይላካሉ። ጅራፉን ያልቻለ በሰላም አገሩ አይገባም።

በዚህ በቢዋዲ ሱቅ ፖሊሶች የብዙ ምስኪን ስደተኞች መሰባሰቢያ እንደሆነ ያውቃሉ። አብዛኞቹ የመኖሪያ ፍቃድ የሌለን ነን። በዑምራ አካባቢ የገባ ብዙ ስደተኛን ለማስወጣት "ሀ" ብለው የሚጀምሩት ከዚህችው የቡዋ ሱቅ ነው። እኔ ጥሎብኝ ፖሊሶቹን ሳይ ገሀነብ ይመስሉኛል። ገና በሩቁ እንቀጠቀጣለሁ። ሌላው ቢቀር ከምሠራባቸው ሰዎች ጋርም እያለሁ እንደማይዙኝ እርግጠኛም ሆኜ ቀልቤ አይወዳቸውም።

አይሻ ጓደኛዬ ግን አትፈራቸውም። በተለይ መጠውኦች /የሀይማኖት ተከራካሪዎች/ በየመንገዱ እየተዘዋወሩ «ተገጢ ተገጢ ወሸክ» /ፊትሽን ሸፍኚ/ እያሉ የሚጮሁ ሲያሰኛቸው የመኖሪያ ፍቃድ የሚጠይቁ ሳያገባቸው ደርሰው ላገራችን ፖሊስ ነን የሚሉ ደረቆች ናቸው። እነርሱ ከያዙ ጣጣቸው ብዙ ነው። መልካቸውና አለባበሳቸው የተለየ ነው። ከአፍንጫቸው በታች ያለ ፂማቸውን ሙልጭ አድርገው ይላጩና የጉንና ጉን



ፂማቸውንና የአገጫቸውን በጣም ረጅም ያደርጉታል። በጣም አስቂኝ መልክ ይሰጣቸዋል። ጀለቢያቸው ከቁርጭምጪሚታቸው ከፍ ይላል። «ቆጥራ» የሚባለውን ነጭ ሻሽ ያለ ኢገል ያደርጉታል። አይሻ እነዚኞቹን በተለይ በነፍሳቸው ትጫወትባቸዋለች።

አንዴ ስቃወራልን መጠውኦ ይመጣና ኢጋማ /የመኖሪያ ፍቃድ/ ይጠይቃታል። ከየት የመጣላት ሀሳብ እንደሆነ እኔ እንጃ እቅፍ ታደርገውና ልትስመው ስታሞጠሙጥ «እስታፍሩላ» ብሎ ልቡ እስኪወልቅ ሮጠ። ሌላ ቀንም እንዲሁ ፖሊሶች ይይዟትና ኢጋማ ይጠይቋታል። የለኝም ትላቸዋለች ወደ መኪናቸው እንድትገባ ይጠይቋታል። አይሻ «አባያዋን» ታወልቅና በለበሰችው አጭር ጉርድ ቀሚስ ሆና «አገሬ ስለምሄድ ይህንን ድሪቶአችሁን እንኩ» ትልና ትወረውርላቸዋለች። ፖሊሱ ሁኔታዋ አስፈርቶት ለጓደኛው «ይህቺ እብድ ናት ከየት አመጣናት እንላለን ለዚች ሀላፊነት አልወስድም» ይልና አውርዷት አባያዋን ወርውሮላት መጭ ይላል። በሰላም እቤቷ ትመለሳለች . . .።

* * * * * *

ሳሚ የሚባለው ልጅ የሰባህ ዘመድ ከኛ ጋር ሳይፈራ በኛው በሌቶች ክፍል ውስጥ ቁጭ ብሎ ያወራል። እነቅድስትን የሚጠይቁ አንዳንድ የአበሻ ወንዶች

ግን ብዙም ሳይቀመጡ በቁማቸው ይመለሳሉ። ቅድስት እንደነገረችኝ ከሆነ በዚህ አገር ህግ ሴትና ወንድ አንድ ላይ ከተገኙ ጥሩ አይደለም። መኪና ውስጥም ቢሆን አብሮሽ የሚሆነው ወንድ ወይ ባልሽ ወይ ደግሞ ወንድምሽ መሆን አለበት።

ሳሚ ግን ልክ እንደሴት ጓደኞቹን አዘውትሮ እየመጣ ያጫውታል። ቀጭን ሞጣጣ ቢጤ ነው። በክሬም የተለጠለጠ ፊቱ ከውስጥ አመዳም እንደሆነ ያስታውቃል። የሰለለች አንገቱን እንደልማድ ያቅለሰልሳታል። ከፊት ለብቻዋ የተንጠለጠለች ረጂም ፀጉር አለችው። ደማቅ የሆኑ ሱሪዎችን ሁልጊዜ ያደርጋል። አንገቱ ላይ ጉልቶ የሚታየው እንቅርት ሲናገርና ሲውጥ ወዲያ ወዲህ እያለ ያስቀይማል። ግን ድምፅ አልሰጠውም። ድምጹ እንደሴት ቀጭን ነው። ደጋግሞ አፉ ውስጥ የሚከታት ረጅም የትንሿ ጣት ጥፍሩን ከሌላው አካሉ አስበልጦ ሳይወዳት አይቀርም። በጣም የተለየ ሰው ነው። ሴታ ሴት ስለሆነ አብሮን ሲሆን ፖሊስ አንፈራም። እሱ ሄድ ሲልላቸው እነ አይሻ «ሙናዬ» ብለው በሴት ስም ያቀማጥሉታል።

አንድ ቀን ማንም በሌለበት ብቻዬን ሆኜ መጣ። እነቅድስትም እያሉ እኔ ሳወራ ፈዞ ስለሚያዳምጠኝ ለኔ የሆነ ስሜት እንዳለው ጥርጣሬ ነበረኝ። አብሬው መቀመጡን ስላልወደድኩት ሻይ ላፈላለት ወደ ወጥ ቤት ገባሁ። ስመለስ የኔኑ አረማመድ ሲለማመድ ያዝኩት። ማሸፍህ ነው ወይ? ስለው አይ አካሄድሽን ብለምድበት በጣም ደስ ይለኛል ብሎኝ እርፍ አለ። ሻይውን ሳመጣለት



ድምፁን ያበልጥ አለሳልሶ አይኑን ስልምልም እያደረገ ከሻይ ጋር የሚቀርበው ጥሩ ቁርስ እንዳለ ጠየቀኝ። እርቦት ይሆን እንዴ? ብዬ ሳስብ አንድ ቀን ሳልዋ ያለችኝን አስታወስኩ። «ይሄ ቀጫጫ ቀላል ሰው እንዳይመስልሽ በጣም ሀብታም ሰው ነው» ያለችኝን። ታዲያ የቤት ምግብ ናፍቆት ይሆናል ብዬ ቁርስ አዘጋጀሁለት። አይኖቹን ያለማፈር ተክሎብኝ እንዳፈጠጠ እነ አይሻ በመሀል መጡልኝ።

እኔና ሳልዋ ብቻችንን ስንሆን

«ሳሚ እናንተ ሳትኖሩ ሲመጣ እፈራዋለሁ።» ስላት ሳልዋ ሶሽ ብላ ሳቀችና «ብቻ ጡቱን ጉንተለኝ እንዳትይ?»

«አይ እንደሱ ሳይሆን አስተያየቱ . . .» አልኳት

«እነ ነገሬ እና አረማመዷን እወደዋለሁ ይላል ለዚያ ይሆናል።» ሳቋን ቀጠለችና

«ግን አትፍሪው ምኑ ያስፈራሻል እ . . . » ብላ የሳሚን ሚስጥር አወራችልኝ።

«ሳሚ እንዲህ የተበላሸው ለገንዘብ ሲል ነው። እርሱን በእጅጉ የሚያፈቅሩ የአረብ ባሎች አሉት። አንድ ጊዜ እሁድ ምሽቱን ከሰባህ ጋር አብሬ ሄጄ መርዶ ተቀምጠን እያለ የሱዳን ሴት ጥምጣም አድርጎ በስሱ ሊፕስቲክ ተቀብቶ ተደብቆ ሊወጣ ሲል አጋጠመኝ። ደንግጬ አየሁት። ለማንም እንዳትነግሪ ብሎኝ ወጣ።

በሚቀጥለው ጊዜ ስላየሁት ነገር አክርሬ ስጠይቀው አልቅሶ ነገረኝ ችግሩን። ሴት ሳይሆን ሴት የመምሰሉን ሚስጥር . . . ለገንዘብ ሲል ወንድነቱን ማጣቱን እና እነዚያ የአረብ ባሉቹ ብዙ ብር ይከፍሉታል ለሴትነቱ።» ብላ ለጆሮዬ ግራ የሆነብኝን የሳሚን ታሪክ አጫወተችኝ። አዘንኩለት።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

እነሳልዋ ቅድስት ሳትኖር ብዙ ውሸት ይነግሩኛል። ቅድስት ካለች ግን ውሸታቸውን የቀጥባሉ። መጀመሪያ ጊዜ ስለወንድ ሲያወሩ አልጋ አናውቅም አሉኝ። እኔም አምኜአቸው እኔም እኮ አላውቅም አልኳቸው። ቅድስት ባለችበት ግን እውነታቸውን አወጡ። የኔን አልጋ አለማወቅ ግን ደጋግሜ ምዬ ነው ያሳመንኳቸው . . . በግድ። ድሮ ድሮ እንደነውር የሚታየው የወንድ ግንኙነት አሁን ደግሞ ተዟዙሮ . . . ጭራሽ ምን ይላሉ . . . «ቆንጆ ነሽ ቁመናሽም ያምራል ታዲያ ምን ሆነሽ ነው ይዘሽው የምትዞሪ» ብለው አሾፉብኝ። በዚያ ሳምንት ብዙ ነገር ሲያወሩ አላዋቂ አድርገው አዩኝ። እንደባላገር . . . ማለቴ ባለባበሴ ያለኝን ችሎታ እስካዛባ ድረስ አስተያየታቸው ልዩ ሆነ። ከጓደኝነቱ ትንሽ ወጣ አደረጉኝ። ሲያወሩ ከቆዩ እኔ ስመጣ ጭጭ ይላሉ። ሁሌ ስለእኔ ወንድ አለማወቅ የሚያወሩ እየመሰለኝ መጣ። ጅዳ



ሆነ እንጂ አዲስ አበባ ቢሆን ይህ እነሱ የፈጠሩብኝ ስሜት ከአንዱ እጅ ነድቶ ይወትፈኝ ነበር። እናቴ «ጓደኛ ይቀይራል» ትል የነበረው እውነቷን ነው። እነርሱን መስዬ ተደባልቄ የሚያወሩትን እንዳወራ ወንድ ማወቅ ፈለግኩ።

በዚያን ሰሞን የተለየ ሴራ እንደሚያሴሩ ሁሉ በጣም ተቀራርበው አፍ ለአፍ ሲያንሶካሹኩ ቅድስት ታዝባቸው «ስለነሱ አልነገርኩሽም በሚቀጥለው ጊዜ በደንብ አወራልሻለሁ ግን ተጠንቀቂ አብረሻቸው የትም እንዳትወጪ» ብላ አስጠነቀቀችኝ ሥራ ከመግባቷ በፊት።

እኔ ቅድስት ያለችውን ሳልሰማ ከነሳልዋ ጋር የሳልዋ አዲስ ቦይፍሬንድ እራት እቤቱ ይጋብዘናል ብለው ሲያሽሞነሙኑኝ ምንም ሳልጠረጥር የሄዱበት ተከተልኳቸው።

እነ አይሻ መኪናው ውስጥ ሲቀሩ እኔና ሳልዋ መምጣታችንን ልናስታውቀው ቀድመን ገባን። የሳልዋ የወንድ ጓደኛ በነጭ ብስ ካኔቴራ በጀልጃላ ሙታንቲ ወገቡን ይዞ እያቃሰተ መጣ። በረጅም ቁመቱ ላይ አገር የሚያክል ቦርጩን ቆንዝሮ በየደቂቃው እያገሳ «አላህምዲሊላ» /ተመስገን/ ይላል። የተባለውን እራት ብቻውን በልቶ መጨረሱን ገመትኩ ከአገሳሱ። ሰውዬው አተኩሮ ማየት የሚገባው ሳልዋን ቢሆንም አይኑን ከእኔ ላይ አልነቅል አለ። ሲናገር ሆዱ እየተነቃነቀ ስላምታ

ሰጠን። አስተያየቱን አፍሬ አቀርቅሬ እያለሁ ደስ የማይሉትን ዝብርቅርቅ የእግር ጣቶቼን አየሁ።

«አሚን ይባላል» አለች ሳልዋ የሰውየውን ስም ስትነግረኝ። ሲጨብጠኝ አይኖቹን አየሁ። ርሁሩሆች ይመስላሉ። ሳልዋ ከገንዘቡ ሌላ የሳባት ነገር አይኖቹ መሆን አለባቸው አልኩ በሀሳቤ።

ሳልዋ እንደመደናገጥ ብላ «እነ አይሻን ልጥራቸው እስከዚያ አሚንን አዋሪው። የሚያጫውትሽ ብዙ ነገር ይኖራል። ጥሩ ሰው ነው» አለችኝና በአረብኛ የኔን መልስ ሳትጠብቅ ጥላኝ ወጣች። ፈገግ አለልኝ። ፈገግታውም ሩህሩህ ነው የሚያስፈራ ሰው አይደለም። ስለዚህ ሳልዋ እንደማትመለስ እኔ ከእርሱ ጋር እንደምቆይ ሲነግረኝ በሳልዋ ብናደድም አልሰጋሁም።

ረጋ ብሎ ልስልስ እጆቹን ሰጠኝና ወደ አንድ ክፍል ወሰደኝ። ግማሽ አረብኛ ግማሽ እንግሊዘኛ ያወራል። ሙሉ ለሙሉ እንግሊዘኛ ባውራ ቢል በደንብ እንደሚናገር ያስታውቃል ብቻ አረቦች እንደዚያ ናቸው አረብነታቸውን ያመልኩታል። ሺ ጊዜ ናሳቸው እስኪዞር ቢማሩ ጀለቢያ /ቀሚሳቸውን/ አያወልቁም። ባህላቸውን አይረግጡም። ቋንቋቸውንም መራቅ አይፈቅዱም። ሩዛቸውን በእጆአቸው አፈስ እያደረጉ እግራቸውን አነባብረው መሬት በመቀመጥ የመመገብ መለያቸውን አይተውም። የምግብ ጠረጴዛ ሹካና ማንኪያ ሞልቶ



ቢተርፋቸውም። ባህላቸውን የሙጥኝ ብለው በሌሎች ባህል ያለመጠመዳቸውን ጥንካሬአቸውን አደንቅላቸዋለሁ።

ክፍሉ ውስጥ እንደገባሁ ነጭና ሰፊው አልጋ አስደነገጠኝ። የፊቴን መቅላት በመስተዋት ማየቴ ይበልጥ ፍርሃቴን አባባሰው አልጋው ላይ ከስምንት በላይ ትራሶች አሉ። በነእሱ አፍና የሚገድለኝ መሰለኝ። ከወደ እጁ ቀጭን ማሰሪያ ያለው ገላን በደንብ የሚያሳይ በፊልም ያየሁት አይነት ስስ የሴት የሌሊት ልብስ እና ተመሳሳይ ከለር ያለው ገመድ መሳይ ነገር አልጋው ላይ ተደርገዋል። ገመድ መሳዩ ነገር ከብዙ አትኩሮት በኋላ ሙታንቲ መሆኑን ማወቄ ፈገግ አስደረገኝ። ከላይ አበባ ተደርጓል. . . ቀይ! ሽቶም።

ከመኝታ ክፍሉ ወደውስጥ ያለው በር ሲከፈት የመታጠቢያ ክፍል ይገኛል። በፍርሃት ተንደርድሬ የመታጠቢያ ክፍል ገባሁና በሩን ዘጋሁ። አሚን በቀልድ አነጋገር ያን የብልግና ስስ ቢጃማ መውደዴን ጠየቀኝ። አሁን ገባኝ ምን ማረግ እንዳለብኝ ላሰላስል በር ስር ተቀመጥኩ። ጊዜ ለማግኘት የባኞውን ውሃ ከፈትኩ። የውሃው ቿቿታ አስጨነቀኝና ዘጋሁት። ወዲያውኑ ፎጣ የያዘ እጁን ዘረጋልኝ። ቀስ ብዬ ሳየው ፊቱን ወደውጪው አድርጓል። እንደሀሳቡ እራቁቴን እንዳያየኝ መሆኑ ነው። ፎጣውን አሾርጬ እስክወጣ ጠበቀኝ። እራቁቴን እንዳያየኝ ማድረጉ ቢያስመሰግነውም ሊያለብሰኝ ያዘጋጀው ቀውጢውን ቀሚስ ምን ይሉታል? እኔ ገላዬን አልታጠብኩም። ልብሴንም አላወለቅሁም። እያነባሁ ብቅ

አልኩፀት:: እግሩ ስር ተንበረከኩና «ነገሩ አልገባኝም አንተ የሳልዋ ጓደኛ መሆንህን ብቻ አውቄ ነው የመጣሁት እንደዚህ ያለ ቀሚስም በህይወቴ ተመኝቼውም ለብሼም አላውቅም እጠላዋለሁ» አልኩት::

ከጉልበቴ ብድግ አድርጎ እንባዬን እየጠረገ

«ኢሽ ሙሽክላ /ምንድን ነው ችግሩ/» ብሎ ረጋ አለ:: ከውስጥ የሚፈታተነውን ወንድነቱን ሲቆጣጠር ታየኝ::

ነገሩን በዝርዝር ሲያስረዳኝ ሁለታችንም ጎን ለጎን አልጋ ላይ ተቀምጠን ነበር::

አሚን ጓደኛው ቤት መደወል ፈልጎ ሲደውል ይሳሳትና የሳልዋ የወንድ ጓደኛ ቤት ይደውላል:: ሳልዋ ድምፁህ ደስ ሲል ብላ ታጠምደዋለች:: «ደስ ካለሽ ማታ ደውይልኝ» ብሎ ስልክ ቁጥሩን ይሰጣታል:: ብቻዋን ስትሆን ትደውልለታለች:: የስልኩ ወሬ ይደራና «እኔ ቢንት /ልጃገረድ/ ነኝ» ትለዋለች:: አሚን ሳይደነቅ «እዚህ አገር ያላገቡ ሴቶች ሁላ ልጃገረዶች ናቸው:: ያለልጃገረ ድነታቸው ከተገኙ የሚጠብቃቸውን ስለሚያውቁ ቢሞቱ አይሳሳቱም» ይላታል:: ቀልጠፍ ትልና «ታዲያ ልጃገረድ ለማየት ጋብቻ ያስፈልግሀል እኔ ያለጋብቻ ባሳይህ ምን ታደርግልኛለህ» ትለዋለች:: ይቋምጥና «የፈለግሺውን» ይላታል:: «ውሽቴን ነው» ስትለው «ልጃገረድ ካልሆንሽማ አልፈልግሽም እንደውም ሁለተኛ አትደውይ ለዚህ ለዚህማ የአውሮፓና የአሜሪካ ሴቶች ምን አሉኝ?» ሳልዋ



ስልኩን እንዳይዘጋ ተለማምጣ የእኔን ሁኔታ ትነግረውና አግባብታ እንድታመጣለት ክፍያ ይዋዋላሉ:: ለእኔም የሆነ ክፍያ እንደሚኖረኝ እርሱ እራሱ ይነግራታል:: በዚህ ምክንያት እኔ አሁን ከማላውቀው ሰው ጋር እገኛለሁ::

የሳልዋ ሥራ ከኔ ይበልጥ ለእርሱ አናደደው:: ሳልስማማ አታለው ስላመጡኝ አዘነልኝ:: ከማዘኑ የተነሳ ብቻ አንዴ ሳመኝ:: ከንፈሮቹ በጣም ይሞቃሉ:: ሰውነቱም በጣም ሲሞቅ ይሰማኛል:: እኔም በጣም ስላመንኩት አስተቃቀፉን አልጠረጠርኩም:: እንደውም በደንብ እንዳምነው እራሳቸውን ለወንድ በገንዘብ መልክ ለሚሰጡ ሴቶች ያለውን አመለካከት አወራልኝ::

«እንደዛ ዓይነት ሴቶች ያስጠሉኛል:: ሴት እዚህ አገር በድብቅ የሆነበት ምክንያት ስለሚያስቀጣ ነው ያ ማለት የኛ ሴቶች ነፃነት አልተሰጣቸውም ሴቶች ነፃነት ሲሰጣቸው በጣም ባለጌዎች ናቸው:: የሀገሬን ሕግ እወደዋለሁ:: ሴት ነፃነት ማግኘት የለባትም:: ነፃነት ቢያገኙ ኖሮ . . . ያ አላህ አሆ! እንደአውሮፓ ሴቶች የገዛ እህቴን እንደዛ ቂጧን ጥላ ስትደንስ! ወንድ ለመሳብ መላ አካሏን ስታቁነጠንጥ . . . እኡዝቢላ!» አይኑን ጨፈን ገለጥ እያደረገ ቀጠለልኝ በአገሩ ሴቶች በጣም እንደሚመካ የአረብ ሴት ቆሸሻ አታውቅም በሕጋችን ከሚያቆሽሻት ነገር እንከላከልላታለን እያለ::

ጥሩ ሰው ነው። እራሱን እየተቆጣጠረ ምንም ሳይነካኝ እቅፍ አድርጐ እንደ አገሩ ሴቶች ውስጡ ከሚያሰቃየው ሙቀት ሲከላከልልኝ አደረ።

ጠዋት ላይ «ይህን የመሰለ ውብ ሌሊት አሳልፌ አላውቅም። እንዲህ እራሴን መግታት የምችል ጀግና ነኝ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። ሴት በጣም ስለምወድ እንኳን አጠገቤ ተኝታ ይቅርና ገና ሳስባት ውስጤ ያተኩሳል። ዛሬ ወንድ ሆኜ ከወንድነቴ ፊት በቆራጥነት ተጋተርኩ። ይታይሽ ለዚያውም ከምታምር ምንም ከማታውቅ ንፁህ ልጅ ጋር አድሬ ቡናማ ገላዋ ልቤን እያቀለጠው. . .»

በነጋታው ሳልዋ ትንሽ እንኳን አፈር ሳትለ ክፍያዋን ልትወስድ መጣች፡ ገና ሲያያት እነዚያ ርህሩህ አይኖች ተቀይረው በንዴት ቀሉ። በጥፊ ጭው አደረጋት። ሳልዋ በምፀት አነጋገር «ዋሸሽኝ ልጃገረድ አልነበርሽም» አለችኝ። እኔ የምላት አልነበረም። አሚን ምላሹን እየጮኸ አስረዳት። ሽቶውንና አበባውን እንዲሁም ጠቅለል ያሉ ብሮች ሰጥቶኝ እቤት ሲያደርሰኝ፦

«ለሁለተኛ ጊዜ እየሳምኩ ባቅፍሽ ደስ ይለኛል። ግን የመጀመሪያው ፈተናዬ በጣም ከብዶኝ ጥርሴን ነክሼ ነው ያለፍኩት። ሁለተኛውን ግን የምችለው አይመስለኝም ስለዚህ እራስሽን ጠብቂ ከነእዚህ ደም ከሌላቸው ጓደኞችሽ» ብሎ ከንፈሬ ላይ የክብረት አሳሳም ሳመኝ።

ለቅድስት የነሳልዋን ሥራ ነገርኳት። ወዲያውኑ የነሳልዋ ጓደኛ ጀሚላ ላይ እርምጃ ወሰደች። እነ አይሻ



እዚህ የሚመጡት እርሷን ፍለጋ ስለሆነ እርሷ መውጣት አለባት ብላ ሻንጣዋን እየገፋች ኮሪደር አደረሰችው።

የዚያን ሳምንት ከልቤ ወድጃቸው ሲሸጡኝ ስላሰቡት ጓደኞቼ ሳስብ ሥራዬን በትክክል መሥራት አልቻልኩም። ይህን አስታኮ የተፈጠረብኝም ፍርሀት ያለሁበትን ሁኔታ በጥርጣሬ እንዳይ አደረገኝ። ገንዘብ አካባቢዬን ሁሉንም ገዝቶ ከሥሩ አድርጐታል።

## ምዕራፍ ሦስት

ከዚህ በፊት በዚህ አመሌ አሪፍ ሥራ እንዳጣሁ ባውቅም አመል አመል ነውና ስደጋግመው ያስደስተኛል:: ታውቂዋለሽ ቀስ ብሎ ሌሎች የሚሉትን የመስማት ልምድ:: ይህ ድርጊቴ ያኔ ትምህርት ቤት ሆኜ ጓደኞቼ ሲያሙኝ እጅ ከፍንጅ ለመያዝ ያስኘ ፅኑ ፍላጐቴ ያሳደረብኝ ሱስ ነው:: ሰዎች እኔ ሳልኖር ስለእኔ የሚሉትን እንደመስማት የሚያጓጓኝ ንግግር የለም:: ትዝ ይልሽ እንደሆን አንቺና የክፍል አለቃችን የነበረው ዳንኤል ስለኔ ስታወሩ ፊታችሁ ከች ብዬ ቀልባችሁን የገፈፍኳችሁ . . . በፊቴ ስለኔ ጥሩ ታወሩ ነበር ከኋላዬ ግን . . . ያን አስታውሼ ቂም ይዤብሻለሁ ለማለት አይደለም:: ልነግርሽ የፈለግኩት ያንን ፀባዬን አልቀየርኩም::

ልክ ፊልም እንደምትቀረፅ የሴት ሰላይ እጄን ወደኋላ አድርጌ ጆሮዬን ከጐን ወዳለው ሳሎን ወረወርኩ::

ትልቋ እመቤቴ ከነባሏ እና ሰሞኑን ምክንያቱን በማላውቀው ጉዳይ ከእኛ ጋር መኖር የጀመረችው ልጃቸው ትንሿ እመቤቴ አረብኛ ፊልም ያያሉ:: አልፎ አልፎ ስለፊልሙ አስተያየት ይሰማል::

የቤቱ ጌታ አፉ ላይ የሚሉጉመው የሺሻ ድምፅ «ቡም ቡም ቡም» ይላል . . . በሳበው ቁጥር:: ሺሻ አረቦች በተለምዶ እንደሲጋራ የሚያጨሱት ባህላዊ ነገር ነው:: ረዘም ብሎ እንደተሠራ የሳሎን ጌጥ ይመስላል:: አናቱ ላይ ትንሽ ገል መሳይ ነገር አለች:: በገሏ ውስጥ የሚጠቀጠቅ መአሰል የሚባል ነገር ከፍራፍሬዎች የሚሠራ ትንባሆ ሲኖር ከበላይ የሚደረገው የከሰል ፍም መአሰሉን እንዲጨስ ያደርገዋል:: ከእቃው ጐን ያለ ቱቦ የሚጨሰውን ጭስ ወደ አጫሹ አፍ ያደርሳል:: ከዕቃው መሀል ያለው ውሃ ነው ጠቀሜታው ያልገባኝ:: እናም ጌታዬ ጭሱን በሳበ ቁጥር እንደሚንተከተክ ውሃ እየተገላበጠ «ቡም ቡም» ሲል ጆሮዬ እየገባ የሰዎቹን ድምፅ እየዋጠ ረበሸኝ::

ለነገሩ ስለኔ አያወሩ! ለምኑ ነው ልፋቱ አያሙኝ ቢያሙኝማ በምን እድሌ::

«አሉዝቢላህ! ይህን ፊልም ያዘጋጀው መሲህ /ክርስቲያን/ መሆን አለበት» ሲል ተሰማኝ ጌታዬ::

«ሙሽሙታለደቢን /አደብ የሌላቸው/» ሚስት ደገፈች:: ምን ዓይነት ፊልም ይሆን? ለማየት ጓጓሁ:: መቼም የብልግና ፊልም መሆን አለበት::

ወደ ክፍሌ እየሮጥኩ ሄድኩና የቴሌቪዥን ጣቢያ እየቀያየርኩ አየሁ:: ምንም ስነ ስርዓት የጣሰ ፊልም አልነበረም:: ሳሎን ያለው ቴሌቪዥን የየትኛውን ጣቢያ እንደሚያስተላልፍ መላ ፈጠርኩ:: ትንፋሼን ዋጥ አደረግኩኝና በቀጥታ ሳሎን ገባሁ::

«ሺሻ ልቀይር እሚ /ጌታዬ/»

የአልፈልግም ምልክት በእጁ ሰጠኝ:: ሙሉ ለሙሉ ክንፉን ዘርግቶ ወደ ቀኝ ፊቱን ያዞረ ቁራ መሳይ ወፍ ያለው ምልክትን ሳይ የንስር /ግብፅ/ ጣቢያ መሆኑን አወቅሁ::

«እንደዚህ መሆን የለበትም:: እንዴት የንስር መንግሥት ይህን ይፈቅዳል?» የሰውዬው ድምፅ

«አስተዘቢላህ! ሴት ረጃል /ወንድን/ እንዴት አትፍቱትኝ ብላ ትፋረዳለች:: አከር ዘመን /የመጨረሻ ዘመን/ ጉ! ጉ!» ሴትየዋ ትልቋ::

«ዘፍኒያ! የክፉ! /ይብቃ/» ብላ ጮኸችና ትንሿ እመቤቱ ወደ ክፍሏ እየሮጠች ገባች:: ልታለቅስ ወደ ክፍሏ እንደገባች ገባኝ:: ሁሉም የአረብ ሴቶች የሚያደርጉት ነው:: የአረብ ሴት እንድታለቅስ ያደረጋት ነገር የተከሰተው ከቤቷ አስር ኪሎ ሜትር ቢርቅ እንኳን ልታለቅስ እየሮጠች ከክፍሏ መግባት አለባት:: ከዛ ወንበር ላይ ወይም ቆማ አታለቅስም:: አልጋ ላይ ዘፍ ብላ በመውደቅ ታለቅሳለች:: ባህል ይሁን ልምድ እኔ እንጃ ወይስ ሲሞላቀቁ. . . ብቻ ሲታዘንም መሞላቀቅ ያምራል እንዴ? እንዚህ ነው የገባኝ:: ክፍሏ ብሄድ አልጋዋ ላይ ተጋድማ ስትንሰቀሰቅ እንደማገኛት እርግጠኛ ነበርኩ:: እንደዚህ ስሜቷን ሊነካ የቻለውን ፊልም ለማየት ቻኑዬ ቴሌቢዥኑን ከፈትኩ::

ፊልሙ ያተኮረው በፍቺ ጉዳይ ላይ ነበር:: አንድ ሴት ለሕግ ባለሙያ ጓደኛዋ ስለበፊት ባሏ እያወራችላት



ወሬዋ እንደትዝታ ሆኖ በፊልሙ ይታያል:: ባልና ሚስቱ እጅግ ይዋደዳሉ:: ባልየው ትንሽ ነገር የሚያናድደው አይነት ነው:: ሚስቱን በጣም እየወደዳት በአንዳንድ ጥቃቅን ጉዳይ ይጨቃጨቃሉ:: ይጮህባታል:: ሚስትየው ረጋ ያለች ነች:: ተው አባክህ ቀዝቀዝ በል እያለች ልታረጋጋው ስትጥር ይታያል:: እናም እንደተለመደው በትንሽ ነገር ሲጨቃጨቁ እራሱን መቆጣጠር ያቅተውና ተሳስቶ ሶስት ጊዜ የፍች ቃሉን ይለዋል::

«ኢንቲ ጣልግ! ጣልግ! ጣልግ!

/አንቺ ተፈትተሻል! ተፈተሻል! ተፈተሻል!» እናም በነዚህ ቃላቶች ባልና ሚስቶቹ ይፋታሉ::

ሚስት ቀላል ሴት አይደለችም:: በሕግ ባለሙያ ጓደኛዋ አመካኝነት ከዚህ በፊት ማንም ሴት ከፍቶት የማያውቀውን ክስ ትከፍታለች::

«ባሌ የፈታኝ በበቂ ምክንያት ስላልሆነ ይመለስልኝ» የሚል

በእስልምና ሀይማኖትና በአረብ ባህል ይህን የሚያክል ነውር የለም:: እናም ይህች ሴት እናት አባቷ ያፍሩባታል:: ሰው ይስቃባታል::

ክሱም በህዝብ ዘንድ የተደገፈ ስላልሆነ ብዙ ሆሆታ አስነሳ:: ሁሉም ወንዶች አልደገፉትም:: ሴቶችም ያልተለመደ ክስ ስለሆነ ፈርተው ስሜታቸውን ደበቁ::

እናም ለኔ ግራ የገባ ፊልም ነበር። ግን ትንሿን እመቤቴን ለምን ነካት?

«ተፋታ ይሆን እንዴ የመጣችው?» ብዬ አሰብኩኝ።

የቀዘቀዘ የሎሚ ጭማቂ ይዤ ያለትዕዛዝ የትንሿ እመቤቴ መኝታ ቤት ገባሁ። እመቤቴ አዝና ፊቷን በመሀረብ ታብሳለች። በርከክ አልኩና «የሎሚ ጭማቂ አመጣሁልሽ ቀዝቃዛ ነው እንዲያቀዘቅዝሽ!»

«እኔ እኮ አልተናደድኩም ብቻ ልቤ ተሰብሯል።» ለቅሶ ቀጠለች። ከእርሷ ጋር እንዳወራ የፈቀደችልኝ ዛሬ ብቻ በመሆኑ የልቧ መሰበር ደስ አለኝ። ልባቸው ሲሰበር የሚያዋሩት ሰው ይፈልጋሉ። ያኔ ብቻ ከፊታቸው እንደሰው ይቆጥሩናል . . . እመቤቶቹ።

«ከባሌ ጋር ተፋትቼ እንደመጣሁ ታውቂያለሽ?»

'የጠረጠርኩት ነገር' አልኩና ራሴን በአሉታ ነቀነቅኩ።

«ባሌ ይወደኛል በዚህ እርግጠኛ ነኝ። እኔም በጣም እወደዋለሁ። እርሱ ህይወቴ ነው። ይገባሻል! አንዳንዴ ሰይጣን በሚዋደዱ ሰዎች መሀል ይገባል አይደል? ሰው ፍፁም አይደለም እናም ፈታኝ»

«ምክንያቱን ልንገርሽ ዝም ብለሽ አዳምጪ። እርሱ እንደራሳችን እንኑር ሲለኝ እኔ ግን የአክስት ልጆቼን ኑሮ እያየሁ እንዲህ እናድርግ እንዲህ እንሥራ እላለሁ።



አይኑን አፍጦ «አይሆንም» ካለ ባሌ አይሆንም ነው። ስለዚህ ወዲያው ነገሩን ረስተን ተቃቅፈን እናድራለን። የፈታኝ እለት የአንዷ አክስቴ ቤት እራት ተጠርተን ልብስ እየቀያየርኩ ነበር። ባሉኝ ልብሶች ሁላ በያንዳንዱ ቀሚሴ አክስቴ ቤት ታይቼአለሁ እና አዲስ መግዛት እንደነበረብኝ ስነግረው እንደ እብድ ሠራው። እኔም ስሜቱን ሳልረዳ ሌሎች ባሎች ለሚስቶቻቸው እንዴት እንደሚጠነቀቁ የሚገዙላቸውን ስጦታዎች ቀሚሶች ገልጬለት እኔ ግን ባሌ ለኔ ግድ እንደሌለው እራሴ እንኳን ግዛልኝ ብዬ ስለው እንደሚጮህ በምሬት ተናገርኩ። ምን እንደነካኝ ሳላውቅ እንደዛ አልኩ እንጂ እንደኔ ባል ለሚስቱ የሚጨነቅ የሚንሰፈሰፍ ባል ጥቂት ነው። በቆምኩበት ጥሎኝ ሄደ። ተከትዬው ሄጄ ነተረከኩት። እንደውም ከጥሪው እንደምንቀር ነግሬው ልብሴን ለማውለቅ ስሞክር ገና ብዙ ቁልፎች መፍታት ይኖርብኝ ነበር። በእርሱ ምርጫ ገዝቶልኝ የነበረ ቀሚሴን ከላይ ጀምሬ ተረተርኩት። ከኋላዬ ፊቱ ደም ለብሶ ተቀያይሮ ሳየው ደነገጥኩ። በእንደዚህ ሁኔታ ፊፅሞ አይቼው አላውቅም።

ትንፋሹን በሀይል ሰበሰበና «አንቺ ጣልግ! ጣልግ! ጣልግ!» አለና በደቂቃ ፈታኝ። ስነቃ እራሴን ሰቼ ሆስፒታል እንደገባሁ ነገሩኝ። ከጐኔ ቆሞ አይቼው ግን እንደባዕድ ተያየን። ተፋተናላ። አይኑ እንባ እንዳዘለ ይህን እንዲያደርግ የገፋፋሁት እራሴው እንደሆንኩ ነገረኝ።

አንዴ በአሳህ ፊት ስለፈታኝ ነገሩ ጊዜ ያለፈበት ሆነ። ለቤተሰቦቼ እንደፈታኝ ሲነግራቸው ክብራቸውን ስለነካ በጣም ጠሉት።

«ይታይሽ ይህ ለፍቺ በቂ ምክንያት ነውን? እንደሌሎች አገሮች ፍቺ በሕግ ቢሆን ጊዜ ይወስድና ባልና ሚስቶቹም ረጋ ብሎ የማሰቢያ በቂ ጊዜ ይኖራቸው ነበር። ፍቺ በአፍ ባይሆን በህግ ቢሆን ባሌ ከንዴቱ መለስ ሲል እንኳን ሊፈታኝ በክፉ አይኑም አያየኝም ነበር። ይመለስልኝ ነበር። በነጋታው ያቅፈኝ ነበር» አለቀሰች።

«የሚወድሽ ከሆነ ለምን እንደገና አያገባሽም?»

«ሊያገባኝ መጥቶ ነበር። ቤተሰቦቼ አልፈቀዱም! እርሱ እንደሚወደኝ በድብቅ ደውሎ ነግሮኛል። አንድ ቀን እንጋባ ይሆናል። ገላዬን ሌላ ሰው እንዲነካ አልፈቅድለትም። እኔ ለእርሱ ተብዬ እንደተፈጠርኩ አውቀዋለሁ። የእርሱ ነኝ።»

«አንቺ ከወደድሺው እርሱም ከወደደሽ ለምን ከቤተሰብ ውጪ አትጋቡም። ቤተሰቦችሽ በኋላ ይቅርታ ያደርጉልሻል። በእኛ አገር ሁለቱ ፍቅረኛሞች ከተዋደዱ የቤተሰብ ውሳኔ እንብዛም አይጠብቁም። ቤተሰብ ቤተሰብ ነው የት ይሄድብሻል ብለሽ ነው!»

«አው! የኛ ሌላ አይነት ሕብረተሰብ ነው። ከቤተሰብ ውጪ ሆነሽ ስታገቢ ቤተሰብሽን ብቻ አይደለም የምትረግጪው። ህብረተሰቡን ረግጠሽ . . . ባህሉን ረግጠሽ እናም ከዚህ ሁሉ ለመውጣት በጣም ጥንካሬ



ያስፈልጋል። እርሱም ቤተሰቦቹን ያጣል እኔም ቤተሰቦቼን አጣለሁ። ይህም ለሁለተኛው ፍቺአችን ምክንያት እንዳይሆን በጣም ስለምፈራ አልደፍርም። በዚያ ላይ እናቴ የልብ በሽተኛ ናት። እኔ እራሴን መዳሬን ስትሰማ ትሞታለች። የማይሞከር ነገር ነው። ይህን ሁኔታ በፊልም አይ እንደሆነ ነው እንጂ ደፍራ ያደረገች አንድ ሱውዲያዊት አትገኝም። አንዳንዴ እናንተን የውጪ ሰዎችን መሆንን እመኛለሁ።»

ባህሉ በትንሿ እመቤቴ የፈጠረባት ትልቅ ችግር ዓይነት ስንቱ በየቤቱ ይኖራል። እንዲያ ከሆነ ታዲያ የአረብ ወንድ ያገባና እፉ እንዳመጣለት «ኢንቲ ጣልግ!» ካለ ሦስት ጊዜ ይህን ሊያስር የቻለ የጋብቻ መስፈርታቸው ጥሩ ስንሰለት ነው ማለት ነው። ሴቷ ከመጋባቷ በፊት የምትጠይቀው የነዋይ ብዛት . . . ታዲያ ያን ያህል ከፍሎ በቀላሉ ትዳሩን የሚያፈርስ እንብዛም ነው። ለነገሩ ሀይማኖታቸውም ጋብቻ ላይ ያለው ተፅእኖ ጥሩ ነው። ችግሩ ሴቷ መፋታት ከፈለገች ነው። ወንዱ ካልፈቀደ እጅግ አስቸጋሪ ነው። ይህ አገር ለወንዶች ያደላል። በጣም ያደላል። ለነገሩ ለተፋታች ሴት ያለው የህብረተሰቡ አመለካከት በጣም ስለሚጫናት መፋታትን እንደሞት እየፈራች ትኖራለች።

«ወይ ጉድ ይህ ሁላ ድሎት ከውስጥ ባዶ ነውን?» ብዬ ገረመኝ። እመቤቴ ላይ የቀናሁባትን ያህል አሳዘነችኝ። ጥሩ ትዝታዋን ቀስቅሼ እመቤቴን ላዘናጋት አሰብኩና

«የአጐትሽ ልጅ ነበር ባልሽ?»

«አይ አልነበረም! አይገርምም?» እውነቱን ለመናገር እኔ የሚገርመኝ ከአጐት ልጃቸው ጋር ጋብቻ የመፈፀሙ ጉዳይ እንጂ ከባዕድ ጋር የመጋባቱ ጉዳይ ምኑ ላይ ሊገርመኝ::

ቀጠለች ንግግሯን «ትንሽ እያለሁ ሁሌ አብሮኝ የሚጫወት የአጐት ልጅ ነበረኝ:: ሁለታችንም ስናድግ እንደምንጋባ ከቤተሰቦቻ ን እንሰማ ስለነበር ስለጋብቻ ያለዕድሜአችን እናወራ ነበር:: «ሳገባሽ እደበድብሽና ደም ብቻ አደርግሻለሁ» ይለኝ ነበር አያስቅም! ታዲያ ስንጫወት የሌሎች ዘመድ ልጆች ከነኩኝ ከቻለ ያግዝልኛል ካልቻለ አብሮኝ ያለቅሳል:: እንዲህ እንዲህ እያለኝ አብረን አድገን እኔ የስምንት ዓመት ልጅ ስሆን እርሱ ደግሞ የአስራ ሁለት ሲሆን መተያየት ተከለከልን:: ከዛ ጀምሮ አባያና ጠረሀ /ረጅም ጥቁር ቀሚስና ሻርፕ/ ለበስኩ:: እርሱንም አይቼው አላውቅም:: እቤት አንዳንዴ ከመጣ እኔ ወደ ክፍሌ እንድገባ እታዘዛለሁ::»

አቋረጥኳትና «እንዴት ከርሱ ጋር ሳትጋቡ ቀራችሁ?»

«አ ታሪኩ ረጅም ነው::»

«ረጅም ታሪክ እወዳለሁ:: ብዙ ጊዜ መጨረሻው አስደሳች ነው» ፊቷን በፈገግታ አበራችልኝ:: ቆንጆ ናት:: ፈገግ ስትል አይኗ እንደመከደን ይልና ቅልብስ ረጃጅም ሽፋሽፍቶቿ ይበልጥ የሚስቡ ይሆናሉ::



«ደግሞ እንደልብ ወለድ ታሪክ አይነት ነው:: የሮሚዮና የጁሌት ታሪክን አንብበሻል. . . ሙች ሙች የኔ ታሪክ ከነርሱ አይተናነስም. . . ደህና ደራሲ ቢያቀናብረው . . . ከየት ልጀምርልሽ አዎ . . . . ታውቂያለሽ አብረውኝ ይማሩ የነበሩ አምስት ጓደኞቼ እንደኔ ሁሉም ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ለአጐታቸው ልጅ እንደሚዳሩ ያውቁት ነበር:: ነገሩ የተለመደ ስለሆነ ወንዱም የአጐቱን ልጅ አላህ ለአዳም ሀዋን እንደፈጠረለት ሁሉ እርሷን ለእርሱ የፈጠረለት መሆኗን ስለሚያምን እርሷን ሌላ ሰው ካገባ እራሱን እንደ ደካማ ሰነፍ የራሱ የሆነ ነገር ሲነጠቅ ዝም ብሎ የሚያይ ፈዛዛ ተደርጐ የተቆጠረ ስለሚመስለው የአጐት ልጁን ቢወዳት ባይወዳት አይለቅም:: ታዲያ ከእነዚያ ጓደኞቼ ጋር ስለወደፊት ባሌ ሳወራ የሚታየኝ እነዚያ በትንሽነቱ ያየኋቸው ምኛምኝ አይኖቹ ስለሆኑ እበሽቅና ንግግሬን አቆማለሁ:: ጓደኞቼ ግን ልቤን እንድከፍትለት ይመክሩኝ ነበር:: ምክንያቱም ሁኔታዬ እየገፋ ልጁን እንዳልጠላና ኑሮዬን እንዳላማርር ያስቡ ስለነበር ነው:: ከኔ በቀር ሁሉም ስለአጐታቸው ልጅ ቀናነት መልክ ሁሌ እያወሩ ራሳቸውን በፍቅር ለማሰር ይሞክራሉ:: እኔ ግን አላህ ሲያማክረኝ እንደማላገባው የነገረኝ ይመስል እንደነሱ አልሞከርኩም:: በተለይ አንዷ ከአጐቷ ልጅ ፍቅር ስለያዛት እራሷን እድለኛ ታደርግ ነበር:: ይህች ልጅ አባቷና አጐቷ ሲጨቃጨቁ ካሁን አሁን ቃላቸውን ያጥፉና የወደፊት ባሌን አጣለሁ እያለች ጭንቀቷን ስትነግረን በሳቅ እንፈነዳ ነበር::»

ባህሏ ከባህሌ ህብረተሰቧ ከእኔ ህብረተሰብ በጣም የተራራቀ ስለሆነ ወሬዋ አዲስና የሚስብ ሆነብኝ። ሳላስበው የእመቤቴ አልጋ ጫፍ ላይ ተቀመጥኩ። በጣም ስህተት ነበር ብቻ በወቅቱ የአልጋ ጫፍ መሆኑ እንጂ የማን አልጋ ለሚለው ቁብ ስላልነበረኝ ተደላደልኩ።

«ባሌ ሙስጠፋን ስተዋወቅ ሊያገባኝ ከነበረው የአጎቴ ልጅ ጋር አባቴ የጋብቻችን ቀን ከአንድ ዓመት በኋላ እንደሚሆን ተስማምተው ለትምህርት ውጪ አገር ሄዶ ነበር።

እኔ ከታናሽ ወንድሜ ትንሿ እህቴ እና ከዳዳ /ሞግዚታቸውን የሚጠሩበት የተለምዶ ስም/ ጋር ሆኜ የገበያ አዳራሽ ውስጥ የሚገኝ የመጫወቻ ቦታ ነበርኩ። ድንገት ሁለት ጉረምሶች ሲሯሯጡ ሙስጠፋን ገፉትና የአይን መነፅሩ ሲፈናጠር እንዴት እንደሆነ ሳላውቀው ራመድ ብዬ ቅልብ አደረግኩት። በፈገግታ አየኝ። አስተያየቱንና አይኖቹን አረሳቸውም። ያለመነፅር በጣም የተዋቡ ናቸው።» ስታወራልኝ የበፊት ባሏን ፊት ለፊት የምታይ ይመስል አይኗን እያባበለች ፈገግ ትላለች አይኗን መልሳ ቡዝዝ ታደርግና ፊካ . . . እዝን እዝን. . . እኔን አታየኝም።

«ከዛ የትም ሳይሄድ እዛው የጫወታ ቦታ ቆም በዓይኑ ሲከተለኝ አየሁ። እኔን ከሌሎች ሴቶች ለመለየት አስቸጋሪ ሲሆንበት በዓይኖቼ እዚህ ጋ ነኝ እለዋለሁ። ብዙ ተያየን። መጨረሻ ላይ ጥቅልል ወረቀት ሲወረውር ዳዳ ሻርፕ ላይ ወደቀ። እየተጣደፈ ወጣ። ወረቀቱን ሲወረውር ያየው እንደሌለ ቃኘት አደረግኩኝና ቶሎ ብዬ ከሞግዚታችን ሻርፕ አነሳሁና ዳዳ ላይ ሙሁኩባት። ለእህት ወንድሜ ወረቀቱ የሚለውን ዋሸቼ «አንቺ ኢንዶኖዥያ ነሽ ወይ?» የሚል እንደሆነ ስገልፅላቸው ከፊታችን ሕፃናት ያጫውት የነበረ አንድ ኢንዶኖዢያዊ ወጣት ላይ ጮሁበት። ነገሩን መሀል ገብቼ አባረድኩ። ትንሿ እህቴ «እንዴት ቢደፍራት ወረቀት ይፅፍላታል» ብላ ለሞግዚታችን ተቆረቆረችና «ሚስኪኗ ዳዳ! ያሚስኪኗ ዳዳ!» ስትል አመሸች።

እየሮጥኩ ባኞ ቤት ገባሁና እየተንቀጠቀጥኩ የወረወረልኝን ወረቀት ስገልጠው የስልክ ቁጥሩንና የምደውልበትን ሰዓት ፅፎ ስሙን ግን አልፃፈም። የዛን እለት ለመጀመሪያ ጊዜ ስለወንድ ያሰብኩበት ቀን ስለነበር ሌሊቱን እንቅልፍ እንቢ አለኝ። ልደውል አልደውል እያልኩ ሳቅማማ ብዙ ቆየሁና ልክ ባለኝ ሰዓት ደወልኩ። ገና ባንድ የስልክ ጥሪ ብቻ ቸኩሎ ማንሳቱ እየጠበቀኝ እንደነበር እርግጠኛ አደረገኝ። ሁለታችንም የምናወራው ጠፍቶን ስንተባተብ ከቆየን በኋላ እንድደውልለት ተቀጣጥረን ስልኩን ዘጋሁ።

ሁሌ ሌሊት የሁሉንም ስልኮች ገመድ እንድትነቅልልኝ ከዳዳ ጋር በገንዘብ ተዋዋልኩ። ሁሉም ሲተኙ እኔ መኝታ ቤቴን ዘግቼ መብራቴ አጥፍቼ እደውልለትና ቢያንስ ለሁለት ሰዓታት እናወራለን። ብዙ

ባወራን ጊዜም እኔም ስለቤተሰቦቼ ስለራሴ እርሱም ስለሁሉም ነገር በግልፅ ስሉተነጋገርን በደንብ ተዋወቅን።»

አቋርጣ የሆነ ነገር ያስታወሰች መሰለችና ፊቷ ቲማቲም መሰለ። የእፍረት ሳቅ ሳቀች «እ . . . » አለችና ልታወራ ያሰበችውን ከአፏ መለሰችው። ይበልጥ አጓጓችኝ። መጓጓቴን ላሳያት አልፈለግኩም። ሀሳቧን ቀየረችና ያሳፈራትን ጉዳይ ነገረችኝ።

«በስልክ ውስጥ ፍቅር ሰራን ታምኚኛለሽ? ፍቅር እንደ አልጋ በስልክ ይሠራል የሚል ሰው ከእኔ በቀር አጋጥሞሽ ያውቃል?»

«እ! እውነቱን ለመናገር አዎ!» እራሴን ነቀነቅኩ። እመቤቱ ከሰው የተለየ ያለችው የግል አጋጣሚዋን የነጠቅኳት ይመስል አይኗን በቁጣ አፈጠጠችና «ውሸታም! ማ?»

«ዜና ላይ አላዳመጥሽም የአሜሪካኑ ፕሬዚዳንት ከከሰሰችው ሴት ጋር ነዋ በስልክ ፍቅር ሰራኝ ብላ የለም!» አልኩ በእርግጠኛነት።

«አ! ያ ሌላ ነገር ነው የኛ ደግሞ ሌላ። ደግሞም ፕሬዚዳንቱ በስልክ የጠለፉበት ሪኮርድ ላይ የተገኘው ቃላት ተራ የፍቅር ቃል ነው። አንድ ሰው ደስ ለምትለው ሴት የሚናገረው ዓይነት ለዚያውም በፍራቻ ቁርጥ ቁርጥ የሚሉ አጫጭር ቃላቶች። ታዲያ ይህችን ቃላት ለፕሬዝዳንቱ ማግኘታቸው በስልክ ፍቅር ሠራ ለሚለው



ቃል በቂ አይደለም። እኔ የምልሽ ሌላውን ዓይነት የፍቅር መሠራራት ነው።»

አሁን እኔ በተራዬ በአግርሞት አይኔን አፈጠጥኩ። እንደሞኝ አፌን ከፍቼ «እ! እንዴት?» አልኩ

«መጀመሪያ የለበስነውን ልብስ በደንብ እንነጋገራለን። ከዛ ዓይናችንን ጨፍነን አንዱ ያንዱን እንደሚያወልቅ ዓይነት የየራሳችንን ልብስ በቀስታ እናወልቃለን. . . እየተንሾካሾክን። እራቁቴን ስሆን ከፊቴ አገኘዋለሁ። በጨለማ ሲዳብሰኝ ይሰማኛል። በለስለስ ድምፅ የቱጋ ልንካሽ ይለኛል ሳላፍር ወደሚዳብሰኝ ቦታ እመራዋለሁ። ነካሁሽ ይለኛል ይነካኛል። ሁለታችንም የእውነት በስሜት እንዋጣለን. . . እንጨነቃለን. . . እንሙሀለን። ሰውነቴ በሙሉ ሀይሉ ሲፈልገው ይሰማኛል። ናልኝ ብዬ አለቅሳለሁ። እጮሃለሁ በፊት የማላውቃቸውን ዓይነት ደስ የሚሉ የሲቃ ድምፆችን ከራሴው አፍ እሰማለሁ። ሌላ እሆናለሁ። የምር እረካለሁ። ሰውነቴ ሊያገኝ የፈለገውን ሁሉ ያገኘ ይመስለኛል። እደሰታለሁ። ከዛም ከመተኛቴ በፊት ዛሬ ሌሊት ውብ ነበርሽ ይለኛል። እንዳየኝ. . . እንደነካኝ ሁሉ ግን ግን እንዲነካኝ እንዲያየኝ እረዳዋለሁ። የሰውነት ክፍሌን ሳልዋሽ በምችለው ቋንቋ ነግሬዋለሁ። እርሱም እርቃኑን ምን እንደሚመስል ሊነግረኝ ሞክሯል። ንገሪኝ እብዶች አይደለን? ንገሪኝ በየትኛው የፍቅር መዝገብ ይህን የመሰለ ተመዝግቦአል . . . ኡፍ እወደዋለሁ።» በእጇ ልቧን ተጫነች።

«ይህ ልዩ ግንኙነታችንን በሳምንት ሁለቴ ሦስቴ እያዳበርነው ሄድንና ሁሉም ነገር ቀላል ሆነልን።

አንድ ቀን ፊቴን ሊያይ እንደሚፈልግ ነገረኝ። እኔም ላየው እፈልግ ስለነበር ለመተያየት ዘዴ ቀየስን። ከዳዳ ጋር የገበያ ቦታ ለመሄድ አስፈቅጄ በተቃጠርነው ሰዓትና ቦታ ተገኘሁ። እርሱም ከሩቅ ሲከተለኝ አየሁ። እንዲያውቀኝ ከአባያዬ በላይ እንደባላገር ነጭ ቦርሳ አንጠልጥዬ ነበር። እንደተነጋገርነው ሰው ወደማይበዛበት ቦታ ሄድንና እንዳቀድነው እርሱ ከፊት ለፊቴ ሲመጣ ሻርፔን የማስተካክል መስዬ ፊቴን ሙሉ ለሙሉ ገለጥኩለት። አየኝ። ሄደ።

በደውልለት ምን ያህል ቆንጆ እንደሆንኩ ደጋግሞ እየነገረኝ የተለየ ፍቅር ሰራን።

ቶሎ ቶሎ ለመተያየቱ የግድ ዘዴ መቀየስ ነበረብን። ወፍራሟ እህቱ መሰላል ሆነችን።

ውፍረቷን ለመቀነስ በየቀኑ የስፖርት ቤት ትሄድ ነበር። እኔም ለቤተሰቤ ሰውነቴን ለማጠንከር ስፖርት መሥራት እንዳለብኝ አሳመንኩና እህቱ የምትሄድበት ስፖርት ቤት አባል ሆንኩ።

በተፈጥሮዬ ስፖርት በጣም ብጠላም የሰውነት አቋሜ ስፖርት ከሚሠሩት ያማረ ነው . . እንደምታይው ግን ለእርሱ ስል ትንፋሼ እስኪያጥር ስፖርት ሠራሁ።



ወፍራሟ እህቱ ዝጋታምና ከሰው የማይገጥም የተለየ ፀባይ ስላላት እርሷን ጓደኛ ለማድረግ ወር ሙሉ ፈጀብኝ። ለዚያውም በጣም ስለተለማመጥኳት እንደገረዷ 'ያን ስጪኝ ይሄን ግፊ ይህን ሳቢ' እያለች አሰለቸችኝ።

ጓደኛ ከሆንን በኋላም ጓደኝነታችን እስከ ስፖርት ቤቱ ደጃፍ ድረስ ብቻ ሆነ። በር ላይ ወንድሟ ቆሞ ይጠብቃታል።

እኔም ለማየት ለዚያች አጭር የዓይን ንግግር ስል ሰውነቴ የማይፈልገውን ስፖርት በግድ አሠራዋለሁ። ማታ ስደውልለት ስለእብደታችን እያወራን ለሊቱን እንስቃለን።

ሁኔታው ቀጥሎ ሲነካኝ ተመኘ። ይህ እንዴት ይሆናል አልኩት ለዚህም መንገድ አላጣንም። አብረን ሌሊቱን ዘየድን።

እኔም ስፖርት ቤት ከመሄዴ በፊት ጣቶቼን በሚያለሰልስ ክሬም ዘፍዝፌ ጥፍሮቼን በሚያምር የጥፍር ቀለም አስዋብኳቸው። ሹፌሬን ዘግይቶ እንዲመጣ ገንዘብ ስለሰጠሁት ከጓደኛዬ ጋር ከስፖርት ቤቱ ስንወጣ በር ላይ አላገኘሁትም።

ጓደኛዬን ሹፌሬ እስኪመጣ አብራኝ እንድትቆም ጠይቄአት እኛ የገመትነውን ጥያቄ ጠየቀችኝ። 'እናድርስሽ?' ለደግነቷ እያመሰገንኳት በደስታ የፍቅሬ መኪና ውስጥ ገባሁ። እንደተነጋገርነው እጆቼን የፊት ወንበር ላይ እንደቀልድ ሳስቀምጥ የኋላ ማርሽ አስገብቶ

ወደ ኋላ ሊያይ እንደመዞር አለና የወንበር ድጋፍ ላይ የነበሩትን ጣቶቼን ጫን ሲላቸው መላ አካላቴ ሲነድ ተሰማኝ::

ንገሪኝ እስቲ ሮሚዮ ጁሊየትን ሲስማት እንደኔ የተሰማት ይመስልሻል?! በጭራሽ! የአለም አሳሳሞች ያህል ሊመስጡ አይችሉም:: ነፍሴ ጥላኝ ሄዳ ነፍሱን ያመጣችልኝ መሰለኝ:: በትንፋሹ ተነፈስኩ::

እህቱ ደንግጣ ወንድሟ ሳያስብ እንደነካኝ ስላሰበች ይቅርታ ጠየቀችኝ:: የምትለው ጠፍቷት እየተንተባተበች 'እጅሽን የፊት ወንበር ላይ ማስቀመጥሽን አላየም:: ይህንን ጉዳይ ለማንም አትናገሪ:: ወንድሜ ስነ ስርዓት ያለው ሰው ነው::' አለችኝ::

የተሸፈነ ፊቴ በደስታ እንደፈነደቀ ጥፋተኛዋ እኔ እንደሆንኩና ነገሩን እንድትረሳ ነግሬአት እቤት አደረሱኝ:: ሹፌሩ ላይ በእናቴ ፊት ለይምሰል ጮኽኩበትና እናቴም የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጠችው:: ነገሩ ሳይታወቅብኝ የምወደውን ወንድ አካል ነካሁ::

በዓመቱ መጨረሻ በሙቀቱ ጊዜ ሁልጊዜ ወደ ውጭ አገር ከቤተሰቤ ጋር መሄዱ የተለመደ ስለሆነ ይህን ጊዜ ጠብቄ ለንደን እንደምንሄድ ነገርኩት:: እዛ በሄድን በሳምንቱ ለእኔ ሲል እዛ ድረስ መጣ::

ለንደን እያለን ከእናቴና እህቴ ተለይቼ ለመውጣት ብሞክርም የማይሆን ሆነ:: በስልክም እንደበፊቱ ፍቅር መሥራት አልቻልንም:: ላብድ ደረስኩ: ደውዬ እዚያው ለንደን ከእርሱ ጋር ለመቅረት እንደምፈልግ ነገርኩት:: ይሁ የማይሞከር ነገር ነው ረጋ በይ እገባሻለሁ' አለኝ:: ቤለጋብቻ ሳስብ ፈራሁ:: አባቴ ቃሉን የማያጥፍ ከባድ ሰው ስለሆነና ያጨኝን የወንድሙን ልጅ በጣም ስለሚወድ ጋብቻችንን እንደማይቀበል እርግጠኛ ነበርኩ::

እንደምንም አንድ ቀን ካለንበት ሳንርቅ ተደብቆ እንዲያየኝ በደንብ ተነጋግረን እየፈራሁ ከዳዳ ጋር ተደብቄ ወጥቼ እንደተባባልነው አባያና ሻርፔን አወለቅኩና ቆምኩ:: ካንድ በኩል የካሜራ ብልጭታ አየሁ:: ፎቶ እንዳነሳኝ ሳረጋግጥ አባያዬን ልለብስ ስል ድንገት እናቴ እራሷን ይዛ እየሮጠች መጣች:: ፀጉሬን ጨምድዳ አስለበሰችኝ:: እናቴን እንደዛ ስትሆን አይቼአት አላውቅም:: የዛን እለት 'ልጅሽ ሸረሞጠች' እንደተባለች እናት ታማ ተኛች:: ደጋግሜ እንድሰግድ አስገደደችኝ:: ለአባቴ 'ልጃችን አበደች እንደ አውሮፓዎቹ ስድ ሴቶች እራቁቷን ሄደችልህ:: ፀጉሯን ከፈተች:: ደግነቱ ማንም ሳያያት አንቄ መለስኳት:: ልጅህ በገዛ እግሯ ገሀነብ ስትገባ ማየት አልፈልግም:: የወንድምህን ልጅ የጋብቻውን ጉዳይ እንዲያፋጥን አስታውቀው:: ቶሎ ታግባና እኔም ልረፍ:: አልፈርድባትም::' ስትለው ሰማሁ::

እረፍታችንን ሳንጨርስ አባያዬን ባወለቅሁ በነጋታው ወደአገራችን መጣን::

ሙስጠፋ የጋብቻችንን ሁኔታ ለቤተሰቦቹ ተናገረ:: የእርሱ አጐት ልጆች በሙሉ ወንዶች ስለሆኑ ቤተሰቦቹ

ከባዕድ ጋር ለሚያደርገው ጋብቻ አልተቃወሙም። ስለቤተሰቦቼ በደንብ አጥንተው ለጋብቻ አባቴን ጠየቁት።

አባቴ ለአጐቴ ልጅ ቃል መግባቱን ገልፆ ጋብቻውን ሳይቀበል ቀረ። በአባቴ ውሳኔ ህይወቴ ወደ እሳት የሚጣል መሰለኝ። ከሙስጠፋ በቀር ማንም ቢሆን ከልቤ ቤር እንደማይደርስ አውቀው ነበር። የአጐቴ ልጅ ነገሩን እንደሰማ ትምህርቱን ትቶ ሊያገባኝ በፍጥነት መጣ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሙስጠፋ ከእርሱ በቀር የማንም እንደማልሆን እየማለ ያሳምነኝ ነበር።

ካጐቴ ልጅ ጋር የተደረገው የሰርግ ቀጠሮ እየቀረበ ሲመጣ እየደወልኩ ማልቀስ ብቻ ሆነ ሥራዬ።

የሰርጌን መቃረብ እንደሞቴ መቅረብ ቆጥሬ ተሰቃየሁ። ሙስጠፋ የአጐቴን አድራሻ ጠይቆ ከወሰደ በኋላ ትንሽም ቢሆን ተስፋ አደረግኩ።

እጅሬ በቀጥታ ሄዶ እንደሚወደኝ ነገረው። የአጐቴ ልጅ እንደእብድ ሠራው። ነገውኑ እንደሚያገባኝ ዛተ። ሙስጠፋ ግን ንግግሩን ቀጥሎ በደንብ እንደሚያውቀኝ ነገረው። ፀጉሬና ፊቴ እየታየ ለንደን ያነሳኝን ፎቶ አሳየው።

እጮኛዬ «ለሌላ ወንድ የታየችን ርካሽ ሴት አላገባም» ብሎ ወደ ትምህርቱ ተመለሰ። ቤተሰቦቼ ላደርስኩባቸው እፍረት ወዲያው ላየኝ ወንድ መዳር ግድ ሆነባቸው። ብዙም ሳይወዱ እኔና ሙስጠፋ ተጋባን።»



ንግግሯን እንደጨረሰች አፈጠጠችብኝ። «አንቺ ምን ላይ ነው የተቀመጥሺው!! ባዋራሽ ገረድነትሽን ረሳሽው ወይ? አልጋዬ ላይ! ከአልጋዬ አሁኑኑ ተነሽ! ውጪ! የአልጋ ልብሱን አንሺና ሌላ ቀይሪ!» ብላ በመጠየፍ አልጋዋንና እኔን አየች። ያን ሁሉ ታሪክ አዳምጬ አብሬአት ባስተሳዝናትም ያው ከዳማ /ገረድ/ ነኝ።

## ምዕራፍ አራት

ቤቱ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ ሳላየው አንድ ቤት ሊኖረው የሚችለውን ስፋት በህልምሽ አልሚ ቢሉኝ እንኳን ላልመው አልችልም። በምንኖርባት አለም ውስጥ ጐረቤታችን የነበሩት የነባንቺ ቤትና የነዚህ ሰዎች ቤትን ያህል ልዩነት ከየት ሊመጣ?! ማማቴ ላይቀር አላይ ቤት እሰማይ ሄጀ አንድዬን እንዳማ ቢፈቀድልኝ መቼም ለሰው ልጆች ልዩነት ከዚህ ሌላ ምን ማስረጃ ሊገኝ!

ከከተማ ከተማ ይጠራሩ ይመስል እናትና ልጅ ባንድ ቤት ሆነው ካንዱ ክፍል ወደሌላኛው በስልክ ያወሩና አንዱ ክፍል ላይ እንዲገናኙ ይቃጠራሉ።

እኔም የተሰጠኝን ጊዜ ጠብቄ ሥራዬን የምጀምረው ባሉቻቸው ሥራ ከሄዱ በኋላ አበቦችን ከነጤዛቸው ቆርጦ አስተካክሎ ለእመቤቴና እናቷ ከእንቅልፍ የመንቂያቸው ሰዓት ሲደርስ አበባ ይዤ በመግባት በደመቀ ፈገግታ «ሰብሀ አልኬር /እንደምን አደሩ/» ብዬ መስኮት በመክፈት ንፁህ አየር አስገብቼ እመቤቶቼን እቀሰቅስና «ጣዛጅ አሲር» /ትኩስ ጭማቂ/ በማቅረብ ነው።

እመቤቴ ለፆሙ ዝግጅት ገና አስራ አምስት ቀን ሲቀረው እናት አባቷ ቤት ገባች. . . እኔም አብሬአት። ይህ የፆም ወቅት ቤተሰብ ለመሰባሰቢያ የመረጠው ወቅት



በመሆኑ ብዙዎቹ ይህን ጊዜ ከቤተሰቦቻቸው ለመቀራረቢያ ከያሉበት ለመሰባሰቢያ ይጠቀሙበታል።

ፆሙ እስኪያበቃ ብቻ የምንቆይ መሆኑ በጀኝ እንጂ የዚህ ቤት ሥራ ሙትት ያደርጋል።

ታዲያ ከጠዋት እስከማታ በዚህ ባህር በሚያክል ቤት ስዋከብ እውልና ወደ ማታ እግሮቼ ይዝላሉ። ለመኝታ ወደተሰጠኝ ክፍል ማምራት እራሱ ትልቅ ሥራ ነው። ብዙ ደረጃዎችን አልፎ የቤቱ አናት ላይ ከተወጣ በኋላ እንደ ቀልድ የተገነቡት ክፍሎች ከወጥ ቤት ሠራተኛ አንስቶ እስከ የፅዳት ሠራተኞች መኝታዎች ናቸው። ሁሉም ሲለፉ ስለሚውል ድንገት ሲገባጠም ብቻ የቻልታ ሰላምታ ተለዋውጦ ክፍሉ ገብቶ ቶሎ አልጋ ላይ ለመውደቅ ይቸኩላል።

እንደዛ ደክሟቸው ቶሎ የማይተኙ ሲያስካኩ የሚያመሹት አዲሶቹ የሥራ ጓደኞቼ ሜሪና ክሬስ ከኔ ቀጥሎ ባለው ክፍል እስከለምዳቸው ድረስ መኝታ ነስተውኝ ነበር።

ሜሪ በጣም ወጣት መስላኝ ነበር። ዕድሜዋን እስከነገረችኝ ጊዜ ድረስ። አጠር ያለች ልጅ እግር ናት። መጀመሪያ ሜሪንና ክሬስን ሳያቸው ክሬስ አሮጊት ከመምሰሏ በቀር ሌላ ምንም የመልክ መለያ የሌላቸው እህትማማቾች መስለውኝ ነበር። በኋላ ግን ክሬስ በሁለታቸው መካከል ስላለው የመልክ ልዩነት አስረዳችኝ።

ስኔ ግን ሁለቱም ፊሊፒኖች ትናንሽ ቅድ አይኖችና ድፍጥጥ አፍንጫ ያላቸው ተመሳሳይ ፍጡሮች ናቸው።

በሥራ በጣም ይተጋገዛሉ። ቋንቋቸውን መስማት በጣም ቢያስጠላኝም የውሸት ለመውደዱ ማስረጃ ብዙ ጊዜ በፈገግታ አያቸዋለሁ። በዕድሜ አነስ ያለችዋ ሜሪ በፍቅር ዓይን ታየኛለች። ክሬስ ግን አይኖቿን በጥላቻ ታለፋቸዋለች። ለዚሁ መፍትሔ እንዲሆነኝ ከሥራዬ ውጪ ክሬስን ልረዳ ብሞክርም ሙከራዬ ሳይሳካ ቀረ። ይልቁንም ይበልጥ እንድርቃት በሁኔታዋ አስረዳችኝ። ችግሩ እርሷን ብቻ እንድርቃት ብቻ ሳይሆን ሜሪንም እንዳናግር አለመፈለጓ ነው።

ሜሪ ከመተኛቷ በፊት እኔ መኝታ ቤት መጥታ ልታሳስቀኝ ስትሞክር ክሬስ ከስነስርዓት ውጪ በሬን በርግዳ ሜሪን ጉትታ መውሰዷን ልማድ አደረገች። ሜሪም እየሳቀች «ምን ያህል ተፈላጊ እንደሆንኩ አየሽ?!» ትልና ተጉትታ ለመወሰዷ ምንም ቅሬታ አይታይባትም። ብቻ በነጋታው ከሥራ መልስ እንደገና ብቅ ብላ ታዋራኛለች። እየቆየን ስንሄድ የሜሪ ወሬ የሚናፍቀኝ አይነት እየሆነ መጣ። ብቻ ብቻ የሜሪ ከልክ ያለፈ ፍቅርና የክሬስ ከልክ ያለፈ ጥላቻ ምክንያቱ አልገባኝ አለ።

ሜሪ ስለህዝቦቿ ብዙ አወራችልኝ። ስለአረብኛ ሙዚቃ ያላትን አስተሳሰብ ግን ተቃወምኩ . . . ስለወንድ ደግሞ የተለየ አገላለፅ አላት።



ቴፔ የሚጫወተውን ዘፈን ፀጥ ብላ ስትሰማ ቆየችና

«ታውቂያለሽ! ይህን ዘፈን ብዙ ጊዜ ስምቼዋለሁ ከሌሎች አረብኛ ሙዚቃዎች ይህ ደስ ይለኛል። የኛ ሙዚቃ ቅንብር ቢበዛ የሰባት ሰዎች ሥራ ነው። አረቦቹ ግን ድርድራቸው ለቁጥር ያስቸግራል። ቫዩሊናቸውን እንቀው የሚወዘውዙ ብዙዎች ናቸው። ይህ ሁሉ አንድ ድንዙዝ ሙዚቃ ለመፍጠር ነው።» ሳቀች።

« እ. . . እ. . . አትሳሳቺ! የአረቦቹ የሙዚቃ ቅምር ጥልቅ ነው። ጥልቀቱን ለማየት ቃናውን ለማጣጣም ትዕግስት ያስፈልግሻል . . . ፀጥ ብለሽ ማዳመጥ። ከአመት በፊት እኔም አረብኛ ዘፈን ከመስማት ይልቅ ቶሎ ደሜ ገብቶ የሚወዘውዘኝን የአሜሪካኖቹን ወይንም የእንግሊዞችን ሙዚቃ እመርጥ ነበር። ግን አረብኛ ሙዚቃ ጋ ስመጣ ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነብኝ። ብዙ ሰዎች ተደርድረው ቫዮሊንን ሲያናግሩ ዘመናዊ ያለመሆናቸው እንዳይመስልሽ . . . ለሙዚቃ ያላቸው ክብር ነው። በዚያ ላይ እንደኔና እንዳንቺ አገር ቋንቋ እየተከፋፈለ የሚነገር ቋንቋ ስለሌላቸው አንድ መሰረት ባለው ጠንካራ ቋንቋቸው በሙዚቃ ውስጥ ማለት የፈለጉትን በስሌ ስልት ይጠቀማሉ። ስለፍቅር ማለት ቢፈልጉ ብዙ ብዙ የቋንቋ መንገድ አላቸው። ስምና ወርቀ የፍቅር ቃላቶቻቸው ከሙዚቃ ቀመራቸው ጋር ተስማሚ ነው። እስቲ አረብኛ ሙዚቃን ለሳምንት ያህል ስሚ ሙች

ፍቅር ይይዝሻል። የሆነ የተሸፈነ ነገርን በስሜት ለመክፈት እስክትዋትቺ ድረስ ይዞሽ ጭልጥ ይላል።»

የሙዚቃ ገለፃዬን በልዩ መንፈስ ከንፈሯን አፏ ውስጥ ከትታ ስታዳምጥ ቆየችና «ልስልስና ስሜታም እንደሆንሽ አሁን ገና አረጋገጥኩ» አለችኝ።

ባለጌ አገላለፅዋ አዲስ አልሆነብኝም። የሜሪ ቃላቶች ግማሻቸው ከብልግና መዝገበ ቃላት የተወሰዱ ናቸው።

«ገረብ ናር ለጊራ ገረብ ናር ለጊራ /የቅናትን እሳት ሞክር/ ኢሊ ኡሊ ኤ ራይክ አል ሳብሪ /ንገረኝ ንገረኝ አስተያየትህን ለትዕግስቴ/» ትላለች ዘፋኝዋ የቅድሙ ዘፈን ቀጥሏል። ሜሪ አስተያየቷን ለዘፈኑ ትርጉም ሰጠች።

«ሴትዮዋ ባሏ ያስቀናት ነበር። ልታስቀናው ሞከረች። የቅናትን እሳት አስሞከረች። እናም እርሱ ሲያስቀናት ለታገሰችው ትዕግስት ከቀና በኋላ አስተያየቱን ጠየቀች። ግን የዚህ አገር ሴት ይህን ልታደርግ ትችል ይመስልሻል? የት ቦታ? ተከፍታ ፊቷን አሳይታ የቱን ወንድ አስቀንታ ልታስከትል?! የማይሆን ነገር ነው። ዘፈን ብቻ ሆኖ መቅረቱ ያሳዝናል።»

ድንገት ፊቷ ተለውጦ በቁጭት እራሷ ነቀነቀችና ንግግሯን በከረሩ ቃላት ቀጠለች።



«አንዳንዴ ሴቶችን በወንድ ላይ አስነሺና መኪና ባደባባይ ንጅና በሰይፋቸው ተቀጪ ተቀጪ ይለኛል። የወንድ ግዞት አያበቃም . . . በሁሉም አገር። የዚህ አገሩ ግን የተለየ ነው። ማን ነውና ወንድ በተፈላጊነቱና በበላይነቱ በህይወታችን የሚጫወተው?! ወንዶች በጣም እራሳቸውን ይወዳሉ። በጫንቃችን ላይ ሆነው ሁሌ ያለእነርሱ መኖር የማንችል ደካማ ፍጡሮች አድርገው በኃይለኝነታቸው ይመካሉ። ቢሆንም የፊሊፒን ሴቶች ይሻላሉ።»

«የፊሊፒን ሴቶች እራሳቸውን ለወንድ አሳልፈው ካልሰጡ በቀር ለግዞት ግዴታ የለባቸውም። እንደኔ ነፃነታቸውን አውጀው ወንድን ከህይወታቸው ካገለሉ ተገላገሉ ማለት ነው። የዚህ አገር ሴቶች ግን ያሳዝናሉ። እዚህ አገር ገና ስገባ ያስደነገጠኝ ወሬ ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ . . . ሴቶች አይሾፍሩም። መቼም ሴት ሆና መልኳን በማሳየት ፀጉሯን በትና በመኪናዋ መሽከርከሩ የመጀመሪያ ህልሟ ነው። እናም በጥቂቱ መኪና እንኳን መንዳት ተከለከሉ . . . በየትኛው ህግ . . . በወንዶቹ ህግ። ወንዶችን እጠላቸዋለሁ። እኔ ለመፈጠሬ ዋና ምክንያት ወንድ ነው። ለመኖሬ ምክንያት እንዲሆን ግን በፍፁም አልፈቅድም።»

ስለወንድ አዕምሮዋን የመረዘ የህይወት አጋጣሚ እንዳላት ባውቅም እንድትነግረኝ ልጫናት አልፈለግኩም።

«ሜሪ ወንድም እንዳለሽ ባላውቅም አባት እንዳለሽ ግን እርግጠኛ ነኝ ታዲያ አባትሽ ወንድ መሆኑን አትርሺ!»

«ወንድ ስጠላ ቁጥር አንድ ብዬ የጀመርኩት ከአባቴ ነው።»

«አባትሽን?» ፈራኋት። «አዝናለሁ አባትሽ ሳያስከፋሽ አይቀርም።»

«እኔን አይደለም እናቴን ነው። ስለዚህ ማንም ወንድ ወድጀው እራሴን እንደናቴ ልሰጠው አልፈልግም።»

«ወደሽ አታውቂም?»

«አውቃለሁ ግን ሸሸሁት»

«የወንድ ግንኙነት አልነበረሽማ?»

«ነበረኝ ብዙ . . . ግን የሚወዱኝ እነርሱ ነበሩ መጨረሻ ላይ እንድወድህ ልታደርግ አልቻልክም ብዬ ስሜታቸውን ጉድቼ እለያያቸዋለሁ።»

«ህይወትሽን ለምን እንዲህ ታሰቃያለሽ? ከምትጉጂ አቸው ይልቅ ያን የወደድሺውን ባትሸሺ ትልቅ ደስታን ታገኚ ነበር»

«ለወንድ የምትከራከርን ደካማ ሴት እጠላለሁ።»

«ጥይኝ እንጂ ህይወቴን የከበቧት ወንዶች ናቸው። ከአባት ፍቅር ጀምሮ የወንድም ፍቅር ለእኔ በህይወቴ እጅግ ጠቃሚ ነው። በዚያ ላይ ብዙ አልሞከርኩም እንጂ



ወንድ ልቤን ስንጥቅ ያደርጋታል። ደግሞም ወንድ ሁሉ አንድ አይደለም።»

«አዎን ወንዶች ይለያያሉ ግን ባንድ ነገር ብቻ አንድ ናቸው. . . ለኛ ለሴቶች ያላቸው አስተያየት አንድ ነው።»

ሜሪ ለወንድ ያላት ጥላቻ አሁን የደረሰችበት ቦታ ያደርሳታል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። የአባቷንና የእናቷን ታሪክ በዝርዝር ባትነግረኝም የጥላቻዋ መንስኤ አባቷ መሆኑ ነው። ይኸው ያስተዳደጋ ሚስጥር በህይወቷ ገንፍሎ ወጣ።

* * * * * *

የአለባበሷ ጉዳይ ሙቀቱን በተመለከተ እንደሆነ ገመትኩ። አልያም ፊሊፒኖች ሴት ለሴት አይተፋፈሩ ይሆናል . . . እኔ እንጃ። ብቻ ሁኔታዋ ልክ አንድ ለዓመታት የናፈቀችው ፍቅረኛዋ የሚመጣና ልብስ በማወላለቅ እንዳይደክምባት ያሰበች ያስመስላታል. . . እራቁቷን ነች እንዳይባል ብቻ ለይምሰል ቅንጥብጣቦ ጨርቆች ጣል አድርጋለች።

«ሃይ ሜሪ ኬፊክ» አልኳት በጣም ገርማኛለች። «ሙዚቃችንን ወደድሺው ባኞ ቤት እያለሽ እንድትሰሚው

ፈልጌ ነው ጮኽ ያደረግኩት፡፡ በእርግጥ የባኛ ቤት ሙዚቃ ነው፡፡»

«ደስ ይላል ትርጉሙ ባይገባኝም»

ትርጉሙ ከጨረቃ ስትወለጂ አየሁሽ . . . ምናምን . . . የፍቅር ዘፈን ነው፡፡ ባኞ ቤትማ ከሰማሽው የውሀው ሙቀት ይበልጥ ይሰማሻል» ከትናንሽ አይኖቿ አንዱን ረገጥ አደረገች፡፡

ሜሪ ብልግና ማውራት ትወዳለች፡፡ ወሬዋን እኔም አልጠላሁትም፡፡ ብቻ ባለጌ ናት፡፡ ደስ ትላለች፡፡

«ኢትሽ ናይሽ» ሁሉም ፊሊፒኖች መሆናቸው ነው በእንግሊዘኛ ቋንቋ በ'ዘ' ድምፅ 'ሰ' ወይንም 'ሽ'ን ይጠቀማሉ፡፡ የሜሪ እንግሊዘኛም ቅምጥል ያለ ይመስላል፡፡ ትናንሽ አይኖቿ ይበልጥ አናንሰዋል. . . ልጅቷ ምን ነካት?

«ምን ትጠጪያለሽ?» ወደ ፍሪጅ አመራሁ፡፡ ከተጋደመችበት አልጋዬ ላይ ተንጠራርታ ያገለደምኩትን ፎጣ ሳበችብኝ፡፡ አፈርኳት፡፡ ፎጣውን እንድትሰጠኝ ባንድ እጄ እየለመንኩ ስታገላት በሌላው እጄ አንዱ ጡቶቼን አንዱ ጭኔን ለመሸፈን እየጣርኩ ነበር፡፡

እፍረቴ ወደ ንዴት ሲለወጥ ግን እንዲህ አልኳት «ምንድን ነው? አንቺ የሌለሽን የአካል ክፍል ብቻዬን አልያዝኩ፡፡ ደግሞም የሚያሳፍር ገላ የለኝም፡፡ እይኝ ጠግበሽ በደንብ እይኝ!» ጮሁኩባት፡፡



በጣም እየሳቀች «እስኪ ዙሪ፡፡ ከኋ. . .ላሽ አሳይኝ ኡ ኡ. . .» ተንከተከተች፡፡

«ይኸው» ከፊት ለፊቷ ይበልጥ ቀርቤ ተሽከረከርኩ፡፡ ካደግሁ በኋላ ገላዬን እናቴ እንኳን እንዳታይብኝ እጠነቀቅ ነበር፡፡ ከወንዶች መሀል አንድ ሴት ሆኜ ስላደግኩ ነው መሰለኝ እራቁት ከሰው ፊት መቅረቡ እጅግ ከባድ አጋጣሚ ነው ለኔ፡፡

ሳቋ ቀዝቀዝ ሲል ተመለከትኳት፡፡ ሳመሉ ጣል ያደረገችውን ጨርቅ ከላይዋ ላይ ሳብ ሳብ አድርጋ መሬት ጣለችው. . . እርሷም እራቁቷን፡፡

እንደ መዳህ እያለች ነጭ ገላዋን ወደኔ አስጠጋች

«አ! በፍቅርሽ ወድቄአለሁ፡፡ ሳታውቂው የቀረሽ አይመስለኝም፡፡ ካየሁሽ ጀምሮ በፍላጐት ነደድኩ፡፡ ተጠጊኝ፡፡ ነይልኝ፡፡» የማየው ነገር ግራ ገባኝ፡፡ እንዲህ አይነት ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ ሁኔታዋ አስፈራኝ፡፡ ሸሸኋት ተጠጋችኝ ምላሷን ዘርጋ ክትት ስታደርግ ምላሷ ከሰው ዘር ምላሶች ረዝሞ ታየኝ፡፡ ዘገነነኝ፡፡

ሜሪ ፍፁም ተቀይራ እየዳኸች ትጠጋኛለች፡፡ እኔ እሸሻታለሁ. . . ትጠጋለች. . . እሸሻታለሁ፡፡ በጠባቧ መኝታ ቤት ተሽከረከርን፡፡ ግራ ገባኝ፡፡ ከንፈሯ ላይ ማር ያለ ይመስል አስሬ ምጥጥጥ እያደረገች በአገጯ ልክ የተቆረጠ ፀጉሯን ምስቅልቅል ስታደርገው በፍርሀት

ተርበተበትኩ፡፡ ምን ዓይነት ዓለም ውስጥ ልትከተኝ አሰበች? ሰይጣን!፡፡»

«እ! ተቃጠልኩ ቅረቢኝ ውዴ! የኔ ውድ?»

እራሴን ቆፍጠን አድርጌ «ከእኔ ምን ትፈልጊያለሽ? ሜሪ ነገርኩሽ እንዳትጠጊኝ!»

«ገላሽን ሙቀትሽን ልስላሴሽን ወጣትነትሽን ገባሽ? አሁን ምን እንደፈለግኩ፡፡ በጣም ተመኘሁሽ፡፡ ለዛሬ ገላሽን ስጪኝ ወደፊት መንፈስሽንና ልብሽን ትሰጪኛለሽ፡፡ ልብሽ ላይ እንድደርስ መሰላሉቼ እነዚህ ጡቶችሽ ናቸው፡፡ ጫፋቸው ያስጉመጃል ልክ ቸኮሌት ላይ እንደተነከሩ ቼሪዎች ናቸው፡፡

የገዛ ገላዬን እያየሁ «ገላዬን?» አልኩ፡፡

«አዎን ገላሽን አየሽ ጡቶችሽ ይፈልጉኛል፡፡ አላልኩሽም ውስጥሽም ሲነር ይታወቀኛል፡፡ አታፍኚው .»

ፊቴ በሀይል ሞቀኝ፡፡ ምክንያቱ በማፈሬ ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ፈለግኩ፡፡ አፍሬ መሆን አለበት እንጂ ይህ ሰይጣናዊ ስሜት እኔ ውስጥ መወለድ የለበትም፡፡ እራሴን ላሳምን እየጣርኩ ሳለ ሜሪ ደርሳ ያዘችኝ፡፡

አይኗን እና አፍንጫዋን ጨምሮ እንደምርቃት ቁጭ ቁጭ ያለ መልኳና ከአጭር ቁመቷ ጋር ያለው ሚጢጢ ሰውነቷ እንደ ጭራቅ ገዝፎ ኃይልን ተላብሶ ልክ እንደደንዳና ጉረምሳ ጭምቅ ሊያደርገኝ አዕምሮዬ ያልተቀበለውን ወሲብ ሊፈፅምብኝ ከፊቴ ተደቅና እኔ ያለ



ምንም አጋዥ ተስፋ ቆርጬ ካሁን አሁን አነቀኝ እያልኩ የማነባ መሰለኝ፡፡ አዕምሮዬ በከባዱ ፈተና ተሰቃየ፡፡

ፈዝዤ ቆምኩ፡፡ ቀስ ብላ ተንበረከከች፡፡ እግሮቼን ከስር ጀምራ እስከላይ ስታረጥባቸው ተሰማኝ፡፡ ውስጤ ተረበሸ፡፡ ለምን? እርሷም ሴት! እኔም ሴት! ግን ለምን? እኔንጃ!»

«እንዴት እንደምታፈቅሪኝ አስተምርሻለሁ! እ! ቃል እገባልሻለሁ! አዎን በጣም ትሞቂያለሽ ፍቅርሽ እንደ እሳት ነው አዎን አቃጥይኝ አዎን . . . ወደሽዋል አየሽ . . . ወደሽዋል፡፡»

ያበሻ አምላክ መስቀል ይዞ

«ተይ ይህን ሰይጣን ስሜት አትቀበይ፡፡ ህይወትሽን በምድርም በሰማይም ያቆሽሽብሻል፡፡ ተይ!»

ሜሪ ከሌላው ጐን

«ላሳይሽ ያላየሽውን፡፡ ማየት ምን ሊያመጣ ?

አትከስሪም ሞክሪ ደስ ካላለሽ ትተይዋለሽ» ፊቷ ላይ የሚርመሰመሰው ፈገግታ ደስ እንደሚለኝ እርግጠኛ የሆነች ያስመስላታል፡፡

ፊቴን ወደ አበሻ አምላክ ሳዞር እናቴን ወንድሞቼ አገሬው ሁሉ ተሰብስቦ «ቱ በስመአብ ቱ» ይሉኛል፡፡

ሜሪ ነጭ ገላዋን ከፊታቸው ሳታገል ትጋፈጣቸዋለች፡፡

«ኑ እኛ የደረስንበት እናድርሳችሁ»

ከተሰበሰቡት አንዱ «ፐ ይህን ስልጣኔ ማድረግ ነው?»

«ውሻ ለምን? ስማ አንተ አበሻ እራሴን መሆን መፈለጌ ውሻ አያስብለኝም።»

«እንደውም የሴት ውሻ ነሽ»

«ውሻ ውሻ ነው ምን ልዩነት ሊያመጣ። ሴት ሆነ ወንድ አየህ እዚህ ላይ ስረታህ። እናንተ ወንዶች እንፈልጋችሁም ስንላችሁ መቋቋም ያቅታችኋል። እስካሁን ገዛችሁን አሁን ስሜታችንን እንኳን ልንሰጣችሁ አንፈልግም። ምንም አይደላችሁም። ወንዶች ምንም አይደላችሁም።»

የአበሻ አምላክ መስቀሉን እንደያዘ

«ይህን ፀያፍ ነገር ቆሜ የማዳምጠው ላንቺ ስል ነው። ራቁትሽን መቆምሽ ለምንድን ነው? ተይ! ልበሺ ተይ!»

ሜሪ የኔን ፋንታ አፏን ሞልታ ትከራከራለች።

«ራቁቷን ስትሆን ስለምታምር ነዋ። ልብስ መልበሷ ራሷን ልትሸፍን ነው?! ለምን መሸፈን አስፈለጋት። ነፃነቷን ስጣት። ተዋት ትይበት። ደግሞ ብዙ ጊዜ ትሰጣት ይመስል» አፏን አሽሟጠጠች አምላኬ ላይ።



እናቴ እራሷን ደፍታ ስትሄድ አየኋት። ከመሄዷ በፊት ግን «ልጄ እኔ ለዚህ አልላኩሽም። እራስሽን አታበላሺ! አደራሽን ልጄ!» ሁሉም አበሾች እንዳዘኑ ሲወጡ የአበሻ አምላኩም ተሰወረ።

የሜሪ ሰውነቴን መጨምደድ ከሀሳቤ አባነነኝ። ሀሳቤ ርቆ ሄዶ ስለወሰደኝ ምን እያደረገች እንደነበር ከማቃሰቷ በቀር አልተሰማኝም። በስሜት እና በአዕምሮዬ መሀል ለማንም ሳልዳኝ ቀየሁ። አረቦች የልብ ሀሳብና የአዕምሮ ሀሳብ የተለያየ ነው ይላሉ። ልብ ስሜታዊ ሀሳቦች ያመነጫል። አእምሮ ደግሞ ረጋ ያለ ሀሳብ ያመነጫል ባይ ናቸው። እንደኔ ሁለት ሀሳቦች ሲጋጩባቸው «ገልቢ ዋላ አቅሊ» /በልቤ ወይስ በአዕምሮዬ/ ልወስን ይላሉ። ታዲያ እንደሚሉት «ብገልቢ እሰልሚክ /በልቤ ላዋራሽ/ ወይስ «ብአቅሊ»

የልቤ መልስ ደካማ ነው ማየት ፈለግኩ። ሜሪ እንዲህ እንድታቃስት አይኖቿ እንዲያናንሱ እንደ ህፃን እንድትድህ ያደረጋት ሬል ማየት።

የአዕምሮዬ መልስ ፍራቻ ነው። ፍራቻ. . . ከሰው ከባህል ከራሴ ፍራቻ ከሱስ። እራሴን አጥቼ ሌላ ሰው ለመሆን ፍራቻ። ታዲያ ያ ባህሌ ከልሎ ያሳደገኝ መጥፎ ፍሬ እንዳልሆነ አስቦ እንደሆነስ? አዕምሮዬን በግድ ተቀበልልኝ ማለቱ . . . እኔንጃ . . . ይታይሽ ይህ ባህሌን እጅግ የሚያከብረው አዕምሮዬ . . . ከጋብቻ በፊ ያለምንም ዓይነት የአካል ስሜትን አጥብቆ ያወገዘ አ

እደግ ጠንካራ አስተሳሰቤን. . . እ. . . ከዚህ በከፋ መልኩ የሴት ለሴት ግንኙነትን እንዴት እንዲቀበልልኝ ላስገድደው? የአበሻ አምላክ እርዳኝ! እራሴን እንድቆጣጠር አድርገኝ:: መውጣት ከሚያስቸግረኝ ወጥመድ ውስጥ አትክተተኝ እባክህ እርዳኝ::

በዚህ መሀል ወደተበረገደው በር ያየሁት ሜሪን እንዳቀፍኩ ነበር:: አፈርኩ:: ሜሪን ከላዬ ላይ መንጭቄ ወረወርኳት::

ክሬስ የጥላቻ አይኗን እላዬ ላይ እንደተከለች ሜሪን ከወደቀችበት አነሳቻት:: ሜሪ በብስጭት የምትሆነው ጠፋት «ዩ ቢች» /ውሻ/

«ያንቺን ያህል አይደለሁም ሁለተኛ እንዳትጠጊኝ ሰይጣን!»

«እራስሽን ለምን ታታልያለሽ? እ! እየወደድሺው»

«ሜሪ ነገርኩሽ ቆሻሻ ነሽ በጣም!»

«ከየት ነው የመጣሽው? . . . ከጫካ ነው እንዴ? እስካሁን ይህን የማታውቂ የጫካ ሰው. . . ባላገር!» ክሬስ በመሀል ገብታ

«ሁለተኛ ፍቅሬን እንዳትነጥቂኝ ሰማሽ?» የትዕዛዝ ነት::

ያደ የክሬስ ጥላቻ አሁን ገና ገባኝ:: እንድትጠላኝ የሜሪ አይን እኔ ላይ የማረፉ ጉዳይ ነው:: ግን



ምን እያየሁ ነው? ህልም? አንድ ሴት የወንድ ጓደኛዋ ላይ ልትቀና የምትችለው ዓይነት ቅናት?! ወይ ጉድ! ይህን ሁላ አላውቅም ነበር:: ይኸው ይህ ስደቴ አዲስ ክስተትን አስታወቀኝ:: አለማችን ከአለማቸው የተለየ ነው:: አይገጥምም::

ክሬስ ሜሪን እየሳመች አባበለቻት:: በቋንቋቸው ብዙ ነገር ትላት ነበር:: በመሀል እኔ እንድሰማ በእንግሊዘኛ «ምንም ቢሆን እንደኔ የሚወድሽ የሚያውቅሽ አታገኚ! ደግሞም ያገርሽ ልጅ ነኝ:: ለቡኒ ገላዋ እንደሆነ ወደ አገራችን ስንሄድ በ'ቦራካይ' ባህር ዳርቻ ከፀሐይ ስር እተኛለሁ:: የኢሊኢሊ ፀሐይ ለገላዬ አንቺ የምትወጂውን ቡኒ ከለር ይሰጠዋል እ!» ቀስ እያለች ልብሷን አወለቀች::

ሜሪ ድብርቷ ለቀቅ አድርጓት ፊቷ በፊት እንደነበረው የፈካ ሆነ:: ልብስ በማውለቁ ክሬስን ረዳቻት የውስጥ ሱሪዋን በጥርሷ ጉተት እያደረገች እስከታች አወረደችላት:: ሁኔታቸው አናደደኝ::

«ስሙኝ! ለምን አንዳችሁ ሌላችሁን አንተ እያላችሁ አትጠሩም:: በዚህ ዘዴ እራሳችሁን በሚያሳምን መልኩ ማታለል በቻላችሁ ነበር:: ክሬስ ለምን አንቺ ክሪስቶቨር ወይም ክርስቲን አትሆኚም . . . እ አንቺም ሆንሽ ስምሽ ወንድ ለመሆን አመቺ ናችሁ» አይሰሙኝም . . . የት ናቸው?! መልስ አልሰጡኝም:: የገዛ አልጋዬ ላይ ዘፍ ብለው ወደቁ::

«ወይኔ! አልጋዬ ወይኔ ካልጋዬ ተነሱ ተነሱ!» የሰፈረባቸው ሰይጣን አልጋዬ ላይ እንዳይራገፍ በመፍራት ጮሁኩኝ፡፡

በተቻለኝ አቅም ከአልጋዬ ላስነሳቸው ወደነሱ ቀረብኩ ሁሉም ነገር በግልፅ ታየኝ፡፡ የሜሪ ምላስ እኔ ላይ እንደዋለ ሁሉ እርጥበቱና ልስላሴው ተሰማኝ፡፡ ጨኸቴ ጋብ ብሎ የሚያደርጉት ነገር ከአቅሜ በላይ በሆነ መልኩ ሙሰጠኝ፡፡ አብሬአቸው አቃሰትኩ፡፡ መጨረሻ በልቤ አናገርኩሽ፡፡

ጠዋት ሥራ ከመጀመራችን በፊት ዘወትር የቁርስ ጠረጴዛ ላይ እንገናኛለን፡፡ የጠዋት ቁርስ የተለያየ ቢሆንም እኔ የወደድኩት ግን ተቆርጦ በደረቀ ዳቦ ላይ የእንጆሪ ማርማላት በጠረጴዛ ቅቤ ተቀብቶ በመሆኑ እዚህ ቤትም ከመጣሁ ጀምሮ ቁርሴን በደስታ እመገባለሁ፡፡ ታዲያ ሁለቱ ሴቶች እንደዚያ በሆኑ በነጋታው ቁርሴን ጠላሁት፡፡ ከፊት ለፊቴ የሚያስመልስ ሰው እንዳለ ሁሉ ሜሪና ክሬስ የሚጉርሱት ጉርሻ እኔን ወደ ላይ አለኝ፡፡ በሆዴ. . .

«አሁን እንደዛ በሆነችበት አፏ እህል ትከታለች? ቱ!» አልኩ

ሜሪና ክሬስ ሊያናግሩኝ የፈለጉት ነገር እንዳለ ሁሉ «እ!» ይሉና ከአፋቸው ይመልሱታል፡፡ በእርግጥ ስለአልጋዬ መዘባረቅ በጣም ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው ባይ ነኝ፡፡ የእነርሱን መንገድ እንድይዝ የውይይት ሙከራ ከሆነ አሁን ሀሳቤን የሚሰርቅ ስሜት የለም፡፡ ትላንት



የሆነው ነገር በፊቴ የሚዘገንን ጥላ ሆኖአል፡፡ ይልቁንም ወደኔው ንፁህ መንገድ ልስባቸው ሙከራ አደረግኩ፡፡

«ሜሪ! ክሬስ! እኔ እወዳችኋለሁ፡፡ የምትሰሩት ሥራ የሰይጣን ሥራ ነው፡፡ በመፅሐፍ ቅዱስ አታምኑም? ከቻላችሁ በሁለታችሁ ያለውን ወሲባዊ ግንኙነት ተውት፡፡ በጣም የሚያሳፍር ነው፡፡ ካልቻላችሁ ግን ማታ ላይ እኔን አትረብሹኝ ካለሁበት ፀጥተኛ አለም አታውጡኝ፡፡ እንደናንተ መላው ጠፍቶኝ ስሜቴ በላዬ ላይ እንዲመፃደቅብኝ አታድርጉኝ፡፡ እኔን ተውኝ እርሱኝ እሺ፡፡»

ተያዩና ሳቁ፡፡ ክሬስ አፏን ከፍታ ስለሳቀች አፏ ገማኝ፡፡ የአፏን ግማት ለመሸሽ ሁሌ ፊቴን አዙሬ መናገር ነበረብኝ፡፡ አሁን ግን ነገሩ ፊት አዙሮ የሚነገር ባለመሆኑ በሚሉት ነገር ፊት ለፊት ተፋጥጬ መመለስ ስላለብኝ የክሬስን የአፍ ግማት ቻል አደረግኩት፡፡ ድንገት አሰብኩኝ፡፡ የአፏ ግማት ከሁኔታው ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን? የሜሪ አፍ ለምን አልገማም ታዲያ? ሜሪ በቅርብ የጀመረች ከሆነና እየቆየች ስትሄድ ግን መግማት ብትጀምርስ? ማን ያውቃል?!

«አይ ሚስኪኗ ስታሳዝኚ ምንም አታውቂም፡፡ መሬት ክብናት ሲሉሽ እሺ. . . ቫይረስ የበሽታ መነሻ ነው ሲሉሽ . . . እሺ መተኛት ደስ የሚለው ከወንድ ጋር ብቻ ነው ሲሉሽ . . . እሺ ሁሉን . . . እሺ» አለች ሜሪ

ትናንሽ አይኖቿን በማስረዳት አይነት ብልጥጥ አድርጋ:: ንግግር ቀጥላ

«ቫይረስ ለበሽታ መንስኤ ለመሆን ለመመራመሩ እድል ስለሌለሽ እሺ በይ:: ስለሌሎች ሁኔታዎችም መቼም እመኝአቸው:: ይህ ግን የግብረ ስጋ ስሜት ያለው በውስጥሽ በእጅሽ ነው:: ተመራምረሽ ከእውነቱ መድረስ ትችያለሽ»

ንግግሯ ስላልጣመኝ አቋረጥኳት:: ያው ዞራ ብልግና ውስጥ ዘው ነው የሜሪ ነገር:: ባለጌነቷ ዛሬ አልጣመኝም:: እጄን በኩራት አጣምሬ «እንዲህ እንድትሆኑ የሚያደርጋችሁ የነገሮች እውነተኛነት ለማወቅ መመራመር ፈልጋችሁ አይመስለኝም:: ብዙ ነገሮች ምርምር አያስፈልጋቸውም:: ደግሞም የሰው ልጅ አዲስ ነገር ለመፍጠር መመራመር አለበት እንጂ ሌሎች የተመራመሩበትን እውነት ይሁን ውሸት እራሴ ተመራምሬ አውቃለሁ ማለት የለበትም:: ሌሎች በበቂ ምክንያት ምርምራቸውን እስካላዩ ድረስ ማመን ግዴታ ነው:: ይህ የምታደርጉት ነውር ግን ለጊዜው ምርጫ ስለሌላችሁ ስሜታችሁን ማሸነፍ ያቃታች ደካሞች ስለሆናችሁ ብቻ ነው:: ወንድ የማግኘት ዕድላችሁ ሲጠብ እራሳችሁን ታታልላላችሁ:: ያለ ወንድ መኖር እንደማትችሉ ማመን አትፈልጉም:: ወንድ ለህይወታችን ምንም አይደለም ብላችሁ ከእውነታ ትሸሻላችሁ ግን ይኼ ተፈጥሮ መሆኑን አትዘንጉ:: አገራችሁ ስትሄዱ በነፃነት ከወንድ ጋር እንደፈለጋችሁ መሆን ስትችሉ አጉል ስነ



ምግባር ውስጥ እራሳችሁን ለምን ታስቃያላችሁ:: መቼም አካላችሁ ቢደስትም ስህተት በሆነ መንገድ እንደሆነ ህሊናችሁ ያውቀዋል:: ከአንቺና ከክሬስ ይልቅ ሌላ ባልና ሚስቶች የተሻለ ህይወት አላቸው:: በህብረተሰቡ ውስጥ ጥንነት ይመላለሳሉ:: ልጆች ይኖራቸዋል ሀላፊነት ይኖራቸዋል:: በኔ ሀሳብ የሰው ልጅ ከወሲብ ይልቅ እጅግ ብዙ የሚያስደስቱ ነገሮች አሉት:: ሁሉም ነገርኮ ስሜት አይደለም:: በግልፅ ንገሩኝ እስኪ ለቅፅበት ከምታልፈዋ አጭር የስሜት ጊዜ በቀር ሁለታችሁን የሚያስተሳስር ነገር አለ? ባልና ሚስቶች ግን ነገራቸው የተሳሰረ ነው:: ስለዚህ እኔም ስሜቴን እንዲገዛው የምፈልገው ወንድ እንዲሆን ነው:: ቤት እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ:: ልጆች ወልጄ ጥሩ ቤተሰብ ለመመስረት እመኛለሁ:: ህይወቴ በእምነት በባህል በህብረተሰብ የታቀፈች ስትሆን ደስተኛ እሆናለሁ እናም ከእኔ ራቁ!»

ሁለቱም አጨበጨቡ:: ባንድ ድምፅ

«ጥሩ ዘገባ ነው ፕሮፌሰር» ብለው ቀለዱ «ንግግራችንን አንቺን በሰማነው መልኩ ልታደምጪን ፍቃደኛ ነሽ?» አለች ሜሪ እጇን እንደድምፅ ማጉያ ማይክራፎን ጨብጣ በቀልድ መልክ ወደአፏ እያስጠጋች::

እራሴን በእሽታ ነቀነቅኩ::

ሜሪ ቀጠለች እጇን በደስታ እያወናጨፈች «ወሲብ ለሰበሽ ይበርድሻል? አይበርድም አይደል ይሞቃል ስለዚህ ወሲብ የስሜት መናር ነው:: ሙቀት ነው ባጭሩ በንክኪ

ወይም ንክኪን በማሰብ የሚፈጠር ስሜት ነው:: እነዚህ ንክኪዎች በተለያየ ቦታ የተለያየ ደረጃ አላቸው:: ጭኖችሽ ሲነኩ የሚሰማሽ ሙቀት እጅሽ ጫፍ ላይ ስትነኪ ከሚኖረው ሙቀት እጅግ ይበልጣል:: እና ሙቀቶች የተለያየ ቦታ የተለያየ ደረጃ ካላቸው ሴት የቱጋ ስትነካ በጣም ሞቋት ለእርካታ እንደምትጋበዝ ከወንዱ ይልቅ ሴት ታውቃለች:: የቱጋ ስትነካ እንደሚነዝራትም ልታውቅላት የምትችለው እርሷው ሴት ናት እንጂ ወንዱ ሊሆን አይችልም:: ምክንያቱም ሴት ሌላዋን ሴት የምትነካው እራሷ እንዲነኩላት የምትፈልገው ቦታ ነው:: በእርግጥ ለወንዶቹ ቦታዎቹን ማሳወቅ ይቻላል:: ያውቁታልም ምናልባት በተፈጥሮ ቢሆንም አነካካቸው እንደሴቷ ፍፁም አይደለም:: ታዲያ የወንድ አስፈላጊነት ምኑ ላይ ነው:: ከሴት ጋር ከወንድ የበለጠ እርካታ ማግኘት እየተቻለ ደግሞ ወንድ ብዙ ጊዜ በራሱ ስሜት ስለሚገዛ እራሱን ብቻ ሊያዳምጥ ይችላል:: ሴት ግን እንዳንቺው ሴት ነች:: ስሜታችሁ አካላችሁ ይመሳሰላል:: የሚያስጮህሽ ቦታ ያስጮሀታል:: በቀላሉ በስሜት ትግባባላችሁ አንድ ስለሆናችሁ::

ክሬስ ተቀብላ

«ተያት ይህ ምን ይገባታል ያገሯ ባህል ተብትቦአታል»

ሜሪ የክሬስን ንግግር ከምንም ሳትቆጥር ትላንት ባየችኝ አስተያየት እያየችኝ



«ለምን ማታ አትሞክሪም የወንድ ይበልጣል ወይስ የሴት . . . ሞክሪ ከዛ እነሜሪ እውነታቸውን ነው ወይም ውሸታቸውን ነው ትያለሽ ሞክሪ»

«እ!» አልኩና እራሴን ወደ ጠረጴዛው ደፋሁ:: ክሬስ በጥርጣሬ አየችኝና

«ለመሆኑ ከወንድ ጋር ተኝተሽ ታውቂለሽ?»

«ኧረ! አላገባሁም!» መልሴ እንባቸው እስኪፈስ አሳቃቸው::

ክሬስ ደግሞ «ማለቴ ከወንድ ጋር ወሲብ ፈፅመሽ ታውቂያለሽ ወ . . . ይ?» አለች::

በማስረዳት መልኩ ድምፄን ዝቅ አድርጌ «አይ! እኔ ልጃገረድ ነኝ::»

ሁለቱም ከፊት ለፊታቸው ያለ የወረቀት መንዲል ስበው አፋቸውን እያበሱ ተነሱና

«ታዲያ ከመጣሽ ጀምሮ ለምን ታለፉናለሽ? መጀመሪያ ብትነግሪን እኮ የመጀመሪያውን ደረጃ አልፈሽ ከሁለተኛው እንድትገቢ አንንተትትሽም ነበር!» በፌዝ እያዩኝ ጥለውኝ ተቃቅፈው ከኩሽና ወጡ::

ክሬስ መለስ ብላ

«ታዲያ የወንድ ወሲብን ካየሽ በኋላ የሴቱን እንድናሳይሽ ቀጠሮ መያዙን አትርሺ! የጫካ ሰው!» ብላኝ ወጣች:: ክሬስ ከበፊቱ በበለጠ ሁኔታ ጥላቻዋን ቆጠብ

እድርጋ ሰሞኑን ቀረበችኝ። ሜሪም ከበፊቱ ባነሰ ሁኔታ ብዙም ሳትወደኝ እንደሁኔታው ሀይ ትለኛለች እኔም በአዕምሮዬ አዋራሁሽ። ማለቴ «በአቅሌ»



# ምዕራፍ አምስት

መጀመሪያ ስገባ ከዋናው በር ግራና ቀኝ የቆሙ ባለስድስት እጆች አስፈሪ ሰው መሳይ ፍጡሮች በጠቆረ ድንጋይ ተቀርፀው ወደ መቃብር ስፍራ እንኳን ደህና መጡ ይግቡ የሚሉ ይመስል ስድስቱን እጆቻቸውን በየአቅጣጫው ቀስረው ያስበረግጋሉ።

ፀጥ እረጭ ጨለም ያለው ቤት ውስጥ ገብቼ ቆሜ ሳለሁ ድምፅዋ ከአካሏ የበረታ ሰውነቷ ከድምፅዋ እጅግ ድክምክም ያለች ሴት መብራት አብርታ ያለምንም ፈገግታ ለደቂቃዎች አስተዋለችኝ . . . ከላይ እስከታች። ለእርሷ ምን እንደገረማት ባላውቅም እኔ ግን እንደዚህ የድምፅና የአካል ልዩነት አይቼ ስለማላውቅ ይኸው ጉዳይ አስደመመኝ።

«ምን ሂና /በዚህ በኩል/» የሚል ትዕዛዝ ሰጥታኝ ረጅሙን ኮሪደር ተከተልኳት።

ሥራውን ያገኘችልኝ ሴት ባሏ ስለሴትየዋ የነገራትን ሁኔታ አስቀድማ ብትነግረኝም የሴትየዋ አስፈሪነትን በተረት ላይ ከሚነገሩት አስማተኛ ሴቶች በላይ ሆኖ አገኘሁት። ቤቱም እንደመቃብር የከበደ ቀፋፊ ስሜትን የሚፈጥር ነበር።